
ማራዠት

ግጥሞች - ቅጽ ፩



ታደለ ብጡል ክብረት

ፖ.ሣ.ቁ. 5510

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

ከዚህ ገጥም ሰብሰብ ውስጥ በቁንጽልም ሆነ በመሉ አውጥቶ ለማሳተም፣ ለማሠራጨት፣ በማንኛውም መልክ አባዝቶ ለመጠቀም በቅድሚያ ከደራሲው የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠ በሕግ ያስጠይቃል።

All rights reserved


No part of this publication may be reproduced in any form without the written permission of the author.

P.O.Box 5510
Addis Ababa
ETHIOPIA

በማሊ ኢጆንሲ ለሕትመት የተዘጋጀ
1987 ዓ/ም

ማስታወሻ ነቱ

ጥራ፣ ግራ ላሳደገችኝ፣
ግብረ-ገብነት ላስተማረችኝ፣
የሥራን ጥቅም ላሳወቀችኝ፣
ለእናቴ ለወ/ሮ ልብሲቱ መኮንን
እና
እንዲሷ ላሉ እናቶች ሁሉ መታሰቢያ ይሁን።



ማውጫ

ርዕስት	ገጽ
መቅድም	5
መግቢያ	8
ምዕራፍ ፩	
- ትዝብት -	9
ምዕራፍ ፪	
- ፍቅር -	61
ምዕራፍ ፫	
- ግብረ-ገብነት -	81
ምዕራፍ ፬	
- ፖለቲካ -	113
አስተያየት	164

መቅድም

«ማንም ሰው ዳሴት ሳላልሆነ በራሱ ምሉዕ አይደለም» ሲል አንድ አንግሊዛዊ ባለቅኔ ጽፎ ነበር። ይህን ያልበት ምክንያት ሰው በሕብረተሰብ መሐከል በሚኖርበት ዘመን ከመሰሎቹ ተነጥሎ መኖር የማይችል መሆኑን ለማስረዳት መሆኑ ይገባናል።

የግጎበራዊ ኑሮ ተካፋይ ከሆንን ዘንዳ ዳግሞ የጋራ ጥቅምን ለማስከበር፣ የጋራ ፍላጎትን ለማሟላት እንዲሁም ሕብረተሰቡን ሊጎዱ የሚችሉትን መጥፎ ተግባራት ለማስወገድ ተሳትፎ ይጠበቅብናል።

ሰው በሕይወት ጎዳና ሲገሰግስ ብዙ አስደሳችም አሳዛኝም ሁኔታዎች ያጋጥሙታል።

በኑሮ ሒደት ውስጥ የሚያጋጥመትን አመዛዝኖ፣ አመጣጥኖና አስተካክሎ ለመኖር ዳግሞ ከወላጆቹ የወረሰው፣ ከትምህርት ገበታ የተቋደሰው፣ ከአካባቢው የቀሰመው ተጽእኖ እንዲሚያደርጉበት አይጠረጠርም።

ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ ወጣቱ በአጉል ፕሮፖጋንዳ በመመራት በጋጠወጥነት ተወጥሮ መልካም ሥነ ምግባርን አውግዞ፣ ለራሱ እንኳን በማይበጀው መንገድ ሲጓዝ ታይቷል። የዚያ አስከፊ ጊዜ ኑሮና ዋልታ አሁንም በወጣቱ ላይ እያንጃበበ ነው።

የአሁኑ ትውልድ ዘመናዊ ትምህርትና፣ በዚያም ሳቢያ የዕውቀትና የኢኮኖሚ መሻሻል እንዳገኘ ይታወቃል። ይህ የመሻሻል ዕድል ዳግሞ፣ ለባሕል፣ ለግብረ-ገብነትና ለሰው ልጅ ፍቅር እንግዳነት ዳርጓቸዋል ለማለት ይቻላል።

የብሔራችንና የአገራችንን መልካም ልምድና ባሕል ለመቅሰም፣ ኋላ ቀር አስተሳሰቦችን ለማስወገድ እንዲቻል፣ ከሕብረተሰቡ አመራር፣ ከትምህርት ቤት ትምህርት፣ ከስነ ጽሁፍ ምክር ማግኘት ያሻል።

በዚህ ስነ ግጥም መድበል ውስጥ የተጻፉት ቁም ነገር አዘል ስንኞች ያካተታቸው:-

በኑሮ ሒደት ውስጥ ልናጤናቸው የሚገቡትን ትዝብቶችና ሁኔታዎች:-

1/ ትዝብት

የማኅበራዊ ኑሮዋችን ተስተካክሎ ለመኖር፣ መፈቃቀር፣ መጋባትና መዋለድ የተለመደ ሲሆን ውሰብስብነቱን የሚገልጠው:-

2/ ፍቅር

በዓለም ውስጥ የሚከሰቱትን የኑሮ ግብግቦች፣ ሌሎች ፈላስፎች፣ ደራሲያንና፣ ምሁራን እንዲሚተነትኑት ሁሉ በዚህ መድበል ውስጥም የሚገልጸው:-

3/ ግብረገብነት

ዓለምን አበጣብጦ፣ ጦርነት የሚቀሰቅስና ሰላምን የሚያጠፋ፣ የገዢዎች የአምባገነንነት ፖለቲካ የሚተችበት፣ የሚወገዝበትና፣ ጭቁኑ፣ ለመብቱ እንዲቆም የሚቀሰቅሰው:-

4/ ፖለቲካ

በሚባሉት አራት ምዕራፎች ውስጥ ይገኛሉ።

"<u>ግራዝት</u>" የአማርኛ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም:- "ሰው ታሞ ሲሰቃይ ተንሰቅስቆና አምሮ ማልቀስ" ማለት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ግጥሞች፣ ባለፉት አርባ ዓመታት ውስጥ ከጻፍኳቸው ጥቂቶቹ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ በተለይም ፖለቲካ ነክ ቹ፣ ከዚህ በፊት ለ26 ዓመት በስዳት በነበርኩበት ዘመን ውስጥ ስለሀገሬና ስለወገኖቼ ሰቆቃ <u>የአራዝሁዋቸው</u> እንባ ውጤቶች ናቸው። ብዙዎቹ ፖለቲካ ነክ ግጥሞቼ በሔቡዕ ወደ ኢትዮጵያ ይገቡ በነበረት:-

ሀ/ "እንታወግለን"
ለ/ "ሕብረት"
ሐ/ "እውነትን ፍለጋ"

በሚባሉ መጽሔቶቼ ታትመው የተበተኑና እንዲሁም፣ እንዲሰንደቅ ዓላማችን፣ አዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በመሳሰሉት ጋዜጣዎችም ለእትም የበቁት ሌሎች ግጥሞቼ ይገኙባቸዋል።

ይህ የግጥም ስብስብ ሊገመት የሚገባው፣ በስንኙ መሳካት፣ ወይም በጽሑፉ ግጥማዊ ቤት መምታት፣ ሳይሆን ቢያዘው መልዕክት ሊያስተላልፍ የፈለገውን ትምህርታዊ ቁም ነገር ነው።

ከዚህ ግንዛቤ ተነስተው ሊያበረታቱኝ፣ ወይም ሊያርሙኝ ለሚሹ ሁሉ፣ ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሰው አድራሻ ቢጽፉልኝ ከልብ አመሰግናለሁ:-

ፖ.ሣ.ቁ 5510
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ታደለ ብጡል ክብረት
1987 ዓ.ም

መግቢያ

የግወደኛ
የመውቀኛ

የመምከሪያ
የመጸረርያ

ለስነል ቡና ለሃይማኖት
የሚበጅ ምክር ሰብክት

አለያም ለአስክስታ ለፍቅር
ወይም አቅራርቶ ለመፎከር

ዳግሞም ስለሀገር ፖለቲካ
ለመተቸት ለትረካ

የሕዝብ ጭቆናን የአገር ድህነት
ቅኖአላሹን ኑሮ የባሕል ውድመት

ሰቆቃዎች ሁሉ የለርባ ሃምሳ ዓመት
አስቲማ አንቡት ከዚህ "<u>ማራዥት</u>"

ታ.ብክ.

<u>ምዕራፍ ፩</u>

<u>ትዝብት</u>

ማራዥት

አንዳች ምጽሐፍ



ከታደለ ብሙል ከብረት

ምዕራፍ ፩

አስተያየት

ሊቀ ጠበብት 12
ገንገበት 13
የቀን ጨለማ 15
ናውዛ ያናወዘ 16
ገበረና ዘረ 17
ለሀብት እሽቅድድም 18
ሞት 19
የሽማግሌ ጸሎት 20
አቶ ዕገሌ አረፉ 21
ልጁን ያስተምር 24
የዓለም ጣጣ 25
የሐሜት ሱሰኖች 27
ተግባር 28
ዶቦ ቆሎ 29
እንባ 31
ሕግ 32
ሰው መውደድ 33
የባሰ አያምጣ 33
ዳግ ሠርቶ 34
ከፋት 34
ኑሮዋችን 35

ቁልምጫ 35
የሰው ጊንጮች 36
ሕይወት 37
ጎረቤት እንዴ እሳት 38
ሁለት አሀዮች 39
ግምብኖና መምህር 40
ውሸት 41
ቤት አፍራሽ 42
ለምን? 43
ሠርቶ መወቀስ 44
የጠረጴዛ ጨዋታ 45
ግዕድንህን ቅበር 47
ሰላም ለገበረ 48
ጫማ ጠራጊ 50
መዋሸክ 51
ደሮ ጨኸት 52
በሰላም ይዳኙ 53
ይገርማል 54
ሲቪሊያዊ ሀብታም 55
አንጀባ 60

ሊቶ ጠቢብት

መስከረም ሲጠባ ሲወጣ ክረምት
አበባው ሲፈካ እህሉ ሲያሸት

ሚዳ ሽንተረራን ሲሞሉት ልማት
ያስመኖል በሆነኩኝ ሰዓሊ አርቲስት

የጋራውን ውበት የሰማይ ጥራቱን
የዛፉን ማቆጥቆጥ ጀረትም መመላቱን

ያየሩ መዓዛ ማወድ መጣረጩን
ያሰኖል በምልኩኝ መሳል ማስረዳቱን

ከአረንጓዴ፣ ቢጫ ከቀዩ ባንዲራ
ብርቱካን ወይን ጠጅ ሰማያዊ ሃምራ

በቀስተ ደመና ቀለሙ ሲሠራ
ይሆናል አስደሳች ሰውን የሚያኮራ

ሰላቱን ቀለማት አድርጉ መነሻ
ሰንደን ተስፋ አንደሆን ለልብ መረመሻ

የጸረ የሳለ እውነተኛ አበሻ
ይባል ሊቶ ጠቢብት ስሙን ማወደሻ።

መስከረም 1947 ዓ.ም.

ገንገበት

ትምህርት ቤት ሳለን አንድ ልጅ ነበረ
የጣጡን የቋጡን እየተሳለቀ
ብዙ የሚያወራ እየፈጣጠረ

ሁሉን አውቃለሁ ባይ
ዳግም ከዚህ በላይ
ገንገበትነቱ ከራቅ የሚታይ

ከዕለታት አንድ ቀን ከቤድ ገዳብ ዘንቦ
ከያቅ ለመዳን ሰው ተሰብስቦ
በረንዳ ላይ ቁመው ሲያወሩ ቢደቦ

ሲሳሳቁ ሰምቶ እየርጠ መጥቶ
ከወረዉ ሊቋደስ አለመጠን ጓጉቶ
ምንድነው አላቸው መሐላቸው ገበቶ

ከተሰበሰቡት ዋሾ የተባለ
የየረር ተራራ ይታይህ አይዳለ?
አዚያ የሚጯጯ አንድ ነገር አለ?

ብሎ ቢጠይቀው ያንን ገንገበት
አም አንዳዚያ ሲሮጥ በዚያ በዳገት
አይደክመውም እንዴ አስቲግ እዩት?

ብሎ መልስ ቢሰጥ ለዋሾ ቢነግረው
ልለየው አልቻልኩም አውሬ ነው ወይስ ሰው?
እባክህ ንገረን ዘረን አንወቀው?

ግንዝበትም አለ እንዴት አትለዩትም
ቃ ጅብ መሆ ኑን እንዴት አታውቁትም
ወይስ አውቃችሁ ነው እኔ ኑ ለማድከም?

አቶ ዋሾ ዳግሞ እንዲህ ይለዋል
ጠቃጠቆ ነገር ይሽው ይታየኛል
ለኔ እንደሚታየኝ ነብር ይመስለኛል

ግንዝበት ተናደ አንተ ውሸታም
ቃ ጅብ ነው እንጂ ነብር አይደለም
እንስሰ እንስሰ ሲል አይታይህም?

ግንዝበት ዋሾውን ውሸታም ነህ ቢል
ዋሾም ግንዝበትን ዳንቆር ነህ ሲል
ግሊጋሮች ገብተው ሁለቱ መሐል

"አሪ ወንድሞቼ ተው አትጣሉ
ነብርና ጅብን የሚለይ በውሉ
ከዚህ ርቀት ላይ ፍጡር የለም አሉ!"

መስከረም 1948 ዓ.ም.

የቀን ጨለማ

ፀሐይ ስትጠልቅ ጨረቃን ተክታ
ቀኑ ከጨለመ በብርሃንም ፈንታ

ምነዋ ተፈጥሮ እንዲህ ጨከነ
የሰው ልጆች ኑሮ ጨለመ መከነ

መሉዋ ጨረቃ የሌሊት ፋኖስ
ትግ ትግ የሚሉ የኮከብ ሕዋስ

ልክ እንደ ፀሐይ፣ መቀት የሌላቸው
እነሱም እንደ ሰው ቀን ጉዳለባቸው?

ቀውጢ ቀን ጨለማ እየተራዘመ
ስንቱን ቤት አፍርሶ ኑሮን አጣመመ?

ይኸ የቀን ጨለማ የሚያስቆርጥ ተስፋ
በሰው ልጅ ሕይወት ላይ እንዲህ ሲንሰራፋ

መኖር ማየት መስማት ስለሆነ ከባድ
ምነው ከሜንታችን አሁኑ ቢወርድ

በጨለማ ፈንታ ቀን እንዲወጣልን
የፈጠረን አምላክ ምህረት ቢያወርድልን?

1970 ዓ/ም

ናውዝ የናወዝ

ናውዝ የሚያናውዝ ቀምቶ እሚበላ
ሰው ጠልቶ የሚኖር እራሱን የጠላ

የሰው ዘር እንክርዳድ እኾሀ እሚከላ
ምን የባሰ ሊኖር ከዚህ መሰል ሌላ

በዕውቀት ተኩትኩቶ በሥራ ልምድ አድጎ
ቤት ትዳር መሥርቶ ልጅ ወልዶ አሳድጎ

ጠባዩ ያማረ የሚሠራ በጎ
ካልሆነ የሰው ልጅ ለምን ተፈልጎ?

ቢጀርው ዳግ ዳጉን ለመስማት ያሰበ
ክፉ እንዳይናገር ምላሱን ያደበ

ጦርነትን ሸሽቶ ሰላምን ያጀበ
ሰማይ ቤት ይጸድቃል በምድር እያበበ

1951 ዓ/ም

****

ንጉሥ መኳንንት ሀብታም
ከሚማቅቁት በሕመም

አይ ሰው ጤናማ ሰው
መቼ መሻሉን አወቀው!

1951 ዓ/ም

ገበሬና አዝርእቱ

አቀርቅሮ አንገቱን አልቡ ላይ ዶፍቶ
ከምስራቅ ምዕራብ ለመሄድ ተንጋቶ
አዝመራ ሊዘራ በሌሊት ተነስቶ
አየሁ ገበሬውን አዝርዕቱን አንግቶ

በጠንካራ እጁ በትኖ ሲዘራ
ሳያይ ወዷላ ወይም ሳያወራ
ኩሽ ኩሽታ ሳይሰማ ሳያይ አተካራ
ዶንቆሮ ወይ ዕውር ይመስል ነበራ

ጠብ ሲሉ ተሰሙኝ በተራ አዝርዕቱ
እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ብለው ሲዛዛቱ
እንክርዳድ ላይሆኑ በመሉ ሊያሸቱ
ሲግማሉ ሰማሁ ሊሆኑለት ሀብቱ

ያ ኮስታራ ፊቱ ቅጭም ያላለው
ንብረቱና ቤቱ ሁሉም በጠቅላላው
ታየኝ የሚያመርተው ለፍቶ አሚያገኘው
አጭዶ አሚከምረው የሰብል ነደው

ከዚያ መለስ ብዬ ባይ ወዷላየ
ቀይ ጥቁር በግለት ዘርን አየለየ
ከሀብታሞች በቀር ዶሃን ስላላየ
ታዘብኩት አራሴን ሻከረኝ ገላየ

ከነዚያ ከአዝርዕት ከትንሽ ቅንጣት
እንዴምን እንነስ አረጋይ ወጣት?
ምነው የሰው ድካም ብንመለከት
ብንከፍል ለልፋቱ ሳንቀንስበት

1952 ዓ/ም

ለሀብት እሽቅድምድም

ቀን ሲዳክር ውሎ በግጥ በበረደ
ገበረው ያርስና ነጋዴም ነግደ
አዛዡም ታዛዡም ወደሥራው ሄደ
ግታ አቤት ይገባል የየለቅሙን እሂደ

አቤቱ አንዳገባ ሲጀምር ማረፍ
ይዋጣል በሃሰብ ይበራል በክንፍ
ሞረር ያልነበረው ወይንም አንድ አርፍ
ያልግል ገበረው ሊሆን ባለዕልፍ

አንዱም ነጋዴ ባለትንሹ ሱቅ
ይመኛል በአያሌው ለማትረፍ በስንጥቅ
ዳኛና ፀሐፊው መሃይምና ሊቅ
ይፈካከራሉ አንዱ ካንዱ ሊልቅ

አጉል ከመመኘት በሰው ከመቅናት
ለዚህ ዓለም ንዋይ አንቅልፍ ከማጣት
በሐቅ ያልመጣውን ከመሰብሰብ ሀብት
አም ለመሆን ነው መታገል መሞት

የዚህ ዓለም ችግር አነዱም ድካሙ
አላፊ መሆኑን ያወቁ የሰሙ
ለሰው ዳግ ለመሥራት የሚሽቀዳደሙ
ክብረት ለነሱ ነው እስከ ዘላለሙ

1952 ዓ/ም

ሞት

ለሰው ልጅ ወዳጅ ወይንም ጠላት
አንዱ ኔ አስተሳሰብ ስለሆነ ሞት

ደካማና ብርቱ ፈሪና ጉበዝ
መበለት መነኩሴ እንዲሁም ገበዝ

ብሎ አይለይምና ሴት ናት ወይም ወንድ
ሞት በጠራን ጊዜ ስላለ መሔድ

እንዴትብያ በንና ሞቶ ለመቀበር
ክፉት ምቀኝነት ምናለበት ቢቀር?

መብለጥለጡን ትተን ሌላ ሰው ለመጉዳት
ደግሞም ክፉ መሆን በሰው ተንኮል መሥራት

ለሰላም እንቅፋት ለሰው ልጅ እንከርዳድ
ከመሆን ታቅበን ብንኖር በመዋደድ

እና ሞት አማይቀር መሆኑን ተረድተን
ምናለ ብንኖር ከክፉት ታቅበን

የነዲጋጉኹን መተው የማይሞቱ
የነሱን አርዓያ መከተል ነው ስልቱ

ስለዚህ ፍጡራን ሰው ነን የምንል
ፍቅር- ርኅራሄን ለሰው እናድል

ይሽንን ፈጽመን በምንሞት እለት
በራ ክፍት ይሆናል የዚያ የግነት

ጥቅምት 1978 ዓ.ም.

የሸማግሌ ጸሎት

አቤቱ አምላኬ የምታውቅ ሁሉን
ቀን ባለፈ ቁጥር ይብስ ማርጂቴን
ምላሴን ግታልኝ ሃሳቤን ወስን
ክፉ እንዳልናገር ምቀኛ እንዳልሆን

ፍላጎቴን ወስን በዱሌን ቀንስ
የሌላን ሰው ችግር መብለጡን ይብስ
አውቂ አንድሠራ ለሥጋ ለነፍስ
ስጠኝ ትዕግስትን ብርታትን ልልበስ

ሕመሜን ድካሜን ወይንም አርር
በማብር እንዳላሳይ ወይ አፈ ተናጋር
ስሀተቱን አዋቂ ተመልካች አዘውር
አድርገኝ ይቅር ባይ አባክህ ዘንድር

ሊጋስ ትሁት አርገኝ ፍቅርን የሚኖዝ
ጥበብን እንድወድ እንድጠላ ዋዛ
ጠላት እንዳይኖረኝ ወዳጅ እንዳለዝ
ሰው መውደድን ስጠኝ ርህራሄን ልንዛ

የካቲት 1946 ዓ.ም.

አቶ አገሌ ወረፌ

ግብረ ገብነቱ ጎመሌ ያማረ
አቶ አገሌ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ

ጊዜ የሚረጅ ሲሆን ወይም ከባድ ሥራ
ያጋጠመው ሁሉ አገሌን ተጣራ

በጣም አጣዳፊ ሥራ መጥቶብኛል
የምጀምርበት መላ እንኳን ጠፍቶኛል

ይሽው ተከምሯል ተቀምጧል ግና
እኔ የያዝኩትን አልጨረስኩምና

ሥራ እንደበዛብኝ ጠንቅቀህ ታውቃለህ
ስለዚህ አገሌ አግዘኝ አባክህ

ብለው ሲማጸኑ አየሰማ አገሌ
እሺ ልሥራው ይላል ከሆነ አድሌ

ይህ ጌዴኖ አስጠራ የሁሉ ታዛኘ
ዳግና ርህራህ ለፍትሕ ተገኘ

ምጣኮ የቀና ጠባዩ የጌታ
ደከመኝ የማይል የሰው ሁሉ አለኝታ

ቢኖትት ቢማስን ጨርሶ የማይደገመው
ፈገግታ ፊቱ ላይ ዘወትር የሚታየው

ስብሰባ ሲደረግ ኮሚቴ ሲጠራ
ሁሉን የሚያቀናጅ ሁሉን የሚሠራ

በመሥሪያ ቤቱና በየ ድግሱ ቤት
በመኖርያው ይሁን ወይም በ ጉረቤት

እገሌ ተባለ ሁሉን የሚተካ
ሥራን የሚያከብር ክብር እንኳ ቢነካ

ሥራው ከበድ ሲል የሰነፈ ሁሉ
እገሌ ይሥራልን ብለው ተባባሉ

እንኳን መደበኛ መጥፎም ሥራ ቢሆን
ይባል ተጀመረ እገሌ ይሥራልን

ከዚህ ወዲያማ ምኑ ይጠየቃል
የአቶ እገሌ ሥራ ሰው መተካት ሆኖአል!

ሁሉም ሰው አወቀ በአቶ እገሌ አመነ
ያም ይምጣ ምን ይምጣ እሱ ይሥራው ሆነ

ጉዳይ ፈጻሚና መልካም ተላላኪ
አቶ እገሌ ሆነ በወንፈል ተተኪ

ብሎ እየተወራ ስሙ ገነነና
አቶ እገሌ ይሥራው በይፋ ሆነና

ይህ የሁሉ ታዛዥ የሁሉ ተጠሪ
ሕፃን ሽማግሌ ሴት ወንዱን አክባሪ

መሯሯጥ መሥራቱ አታከተውና
አቅሙ ተዳከመ ታመመ በጠና

ጉልበቱ ኹሉ ሳሱ አእምሮውም ዛለ
መናገር አቅቶት ድምጹ እንኳን ሰለለ

መተንፈስ አቅቶት ፍጹም ተዳከመ
አቶ እገሌን መላክ በቃ አከተመ

እንግዲህ እወቁት ከዘረ ጀምሮ
የአናንተን ትዛዝ የሚሰማ ጆሮ

አቶ እገሌ የሚባል በወንፈል ተተኪ
ሞተና ቀበርነው ያንን ተላላኪ

****

የአቶ እገሌ ታሪክ እዚህ አከተመ
ጤና የሆነ ሰው ምንም ያልታመመ

እውቀት ጉልበት ኑሮት መሥራት የሚችል
እገሌን ሊያሠራ ለምንስ ያሻል?

በምጣኔ ሀብቷ አገር የምታድግ
ትምህርት የሚሻሻል የሚበለጸግ

እገሌ ከገሌ ብሎ ሳይመራርጥ
ሁሉም በየፊናው ለሥራ መሯሯጥ

መሆኑን ተረድተን ለገሌ ከመተው
መሥራት እንዳለብን ጠንቅቀን ካወቅነው

አገር ይሻሻላል ሕዝብም ይከበራል
ሰላም በአገራችን መሉ ይሰፍናል

ከዛሬ ጀምሮ ከዚችው ደቂቃ
እገሌ እንዲሠራ መመኘቱ ያብቃ

ስለዚህ እገሌ ይሥራ ከምትሉ
አራሳችሁ ሥሩ ግቡ በወንፈሉ

ሕዳር 1984 ዓ.ም.

ልጁን ያስተምር

በትምህርት ጎዳና ያልተመላለሰ
ዕውቀት በዘር ሐረግ መቼ ተወረሰ,

ረጅም መሆኑን የዕውቀት ጉዳና
ሂደበት ይቅመሰው የፍሬውን ቃና

ዕውቀት ሀብት መሆኑን ለማረጋገጥ
ሥራ ላይ ለማዋል ቁልፉን ይጨብጥ

በዕውቀት በሥራ ተከብሮ እንዲኖር
ሰው ነኝ የሚል ሁሉ ልጁን ያስተምር

መስከረም 1945 ዓ.ም.

የዓለም ጣጣ

የዚህ ዓለም ኑሮ በጣም ያስቸገራል
ገሚሱ ሰው ሲስቅ ገሚሱ ያለቅሳል
ገሚሱ ሲዳሰት ገሚሱ ይቆጣል
አንዱ ሲያመሰግን ሌላው ያሽሟጥጣል

የዚህ ዓለም ኑሮ ጣመ አይታወቅም
ዳጉ በልክ ነው የቀረው ነው እርጉም
ሁሉ ሰው ለማኝ ነው ሰው የለበትም
ሃብታሙ ንፍግ ነው ደሀውም የለውም

የዚህ ዓለም ኑሮ ሁኔል አሰቃቂ
አንዱ እበላ ባይ ነው ሌላውም ሰነቋቂ
አንዱት ዳኛ ይጥፉ ወይንም አዋቂ
ይህን ሁሉ ተንበር ካንገት ላይ አውላቂ?

የዚህ ዓለም ኑሮ የሀብታም መዋኛ
ያታላይ የሌባ ዳግሞም የቀበኛ
የቀጣፊ ዳን ነው ሞምር የጉቦኛ
ዳግሞም ያጎበጎቢ የሰነፍ መናኛ

የዚህ ዓለም ኑሮ መቼም አይጧላ
ጥቂቱ ብልጥ ነው አብዛኛው ተላላ
ጥቂቱ ሰው ሽያጭ ነው አብዛኛው ዳላላ
ቅጥ አጣሹ ኑሮ ምንም የማይሞላ

የዚህ ዓለም ኑሮ የለውም ሚዛን
ጥቂቱ ሲዳሰት የተረፈው ሲያዝን
ብዙው በሕልሙ ሲያይ ያጣውን በዕውን
ይህ ዝበርቅርቅ ኑሮ አስኸመቸ ይሆን?

የዚህ ዓለም ኑሮ ምነው አጣ ተስፋ
ቅናት ምቀኝነት ክፋት እንዲጠፋ
ኩራት እንዲወገድ ችግር እንደይሰፋ
መታረዝ እንዲቀር መራብ እንዲጠፋ

ግራ ይገባኛል አላውቅም መልሱን
ግን ይፈቀድልኝ ልግለጥ ሃሳቤን
ሃኪም መሃንዲሱ ወይም መኮንን
ፀሐፊው መምህሩ ይርሳ ንዋይን

የዓለምን ክንውነት ያመነ ጎልማሳ
ለአገር ለወገኑ እንዲሁም ለጎሳ
ለመሥራት ለመርዳት ታጥቆ የተነሳ
በዕውቀት በጉልበት ያገልግል ሳይሳሳ

ብሰሞት ሲገጥመው ሥራ አደናቃፊ
ይታገሥ ይቻለው ይሁን ሆደ ሰፊ
ሕይወትም ብታጥር ብትሆንም ጋላፊ
አስካለች ይሥራባት ይሁነ ግፍን ገፊ

የሰው መጀመሪያ ደግሞም መጪረሻው
አፈር መሆ ኑንም ምን ጊዜም ካልረሳው
አቻ ሆኖ ይሥራ እንደየቻሉታው
እንዴ ኔ አስተያየት መፍትሔው ይሽው ነው

መጋቢት 1944 ዓ.ም.

የሐሜት ሱሰኞች

የሐሜት ሱሰኞች ወረ ለቃሚዎች
ይህን ወረ ሰመ ለማዝመት የሚመች

የከሳ ስታዮ በሉት ነው ተርቦ
የሚበላው አጥቶ አመሱብ ላይ ቀርቦ

ወፍራም የሆነ እንዲሁ መሳይ የደላው
በሉት ጥጋበኛ ክፉ ሆዳም ነው

ሥራ አጥቶ የሚኖር የሚንከራተትን
በሉ ሰነፍ ሰው ነው የማይረባ ብኩን

ዳህና ሠራተኛ ብርቱ ተጣጣሪ
በሉት ስግብግብ ነው ገንዘብን ቋጣሪ

ለመማር የሚሻን ታታሪ ለዕውቀት
ሰይጣን ጎታች በሉት መምህር የመተት

ዕድል ያላገኘን ትምህርት ለመማር
በሉት ነው ዳንቆሮ ገንገበት ነገር

የሐሜት ሱሰኞች ወረ የምትለቅመ
ለማዝመት የሚመች ይሽን ወረ ሰመ

እገሌ ፈሪ ነው ዳካማ ዳንባራ
ጠጪ ነው ሴሰኛ ረጋጭ ዳንኪራ

ዋሾ ነው ቀጣፊ ሰው የሚያጭበረብር
ብላቸ ሁ በማውራት አደር ሱ ለመንደር

በናንተ አስተያየት በናንተ ግምት
ውርዴት ስለሆነ ሠርቶማ መብላት

በያዳባባ ዩ ለማጥፋት የሰው ስም
ሰውን ለማጋጨት ወንድምን ከወንድም

የሔሜት መኳንንት አበላ ባዮ ቹ
በቅሎ ወሊዴ ቹ ባይ ወራዴ ቹ ዋሾ ቹ

በናንተ አስተያየት ሰው አይታመን
ሁሉ ዴካማና ዋሾና ብኩን

እያሉ ማውራቱ ከሆነ ሥራ ቹ ሁ
ወሬን መቆራኘት ሱስ ከሆነባ ቹ ሁ

የሰው ልጅ በሥራው ስለሚታወቅ
ወሬኛው ሰብቀኛው ከሰው ዘንድ ይራቅ!

መስከረም 1948 ዓ.ም.

ተግባር

ወፍን በላባዋ ነብርን በጥፍሯ
ቁም ነገረኛን ሰው በመልካም ተግባሯ

ሲዶቱ ለማወቅ ከሌላው ፍጡር
ምንም አይሳንም አይኖርም ቸግር

ጎንደር 1953 ዓ.ም.

ደቦ ቆሎ

አንዲት ሰቀላ ቤት ባለ ትንሽ ጊዴ
ውስጧም ሆነ ውጭዋ ፈጽሞ ይልጸዴ

ተከራይተን ስንኖር ከእናቴ ጋር
ነበረብን በጣም ከፍ ያለ ችግር

የክብር ዘበኛው የኔ የአንጀራ አባት
ኮርያ ላይ ሊዋጋ በትዕዛዝ ሲዘምት

ይሰጠን ነበረ ዴሞዙ ተከፍሎ
ለቤት ክራይ ለልብስ ለምግብ ተብሎ

ግና በመሆኑ ገንዘቡ አነስተኛ
ቀኑን ቁጭ ስንል ሌሊቱን ሳንተኛ

እማ ጠላ ስትጠምቅ እኔ ስሸቅል
ከወር ወር ለመድረስ ነበረ ትግል

ይህ ይባስ አለና ዘማቹ አባት
ስንቅ ላኩ አሰ ደቦ ቆሎ አንሶት

ብሎም ስለላክ ሁነኛ ጊዴን
አልተሟለም ግለፍ መርሳት መልዕክቱን

ቀድሞውንም ቢሆን ሳንበላ አስከንጠግብ
የቀን ልብስ የሌለን ሌት የሚዴረብ

ሊሞት ስለሄደ አሰው ሰው አገር
በይሉኝታ ብቻ ይዘጋጅ ጀመር

አስፈላጊዎቹን ገዝተን በያይነቱ
ደቦውም ተቆልቶ ተጋግሮ አንስቱ

ሁሉ ተዘጋጅቶ ቀርቦ በሰፈድ
መሰነቅ ጀመርን በተራ አንድ በአንድ

አንስቱ ተከትቶ ቆሎውም ሲሞላ
አንዲት ደቦ ቆሎ ብትወድቅ ኮለል ብላ

አኔና እናቴ ለቅቀን ከረጢቱን
ያሞን ቅንጣት ልንወስድ መሻማት ጀመርን

እጄ እጄ ላይ ሲያርፍ ላነሳ ስታጣ
ዓይኔ ዓይናጋ ርጠ ሊያይ ይሆን ሊቆጣ?

ሲታጠረ አንዳየሁ ወዲያው ኑ በአንባ
በአራት ዘርፍ ዘነቡ ከዓይኖቿ ስንባ

ጥብቆህን ዘርጋ አንካ በያይነቱ
ምነው ባይሰነቅ ሸረ ምን አባቱ

ብላ ሰጥታ ለኔ አድርጋ አፍስ
ግባች ወዴ ጓዳ ልታለቃቅስ

ጥቅምት 1949 ዓ.ም.

አንባ

ሕፃን ልጅ ሲቆርጠው ሲርበው ሲያለቅስ
ይገርመኝ ነበር አንባ ካይኑ ሲፈስ

ይህ ሕፃን ቆይቶ አድጎ ወጣት ሲሆን
ሲጫወት ሲወድቅ ያነባል አንባውን

ዳግሞም ሲጉረምስ ሲደባደብ ካቻው
የሸንፈቱን ቁጭት ይወጣዋል በአንባው

ለአቅመ አዳም ሲደርስ በፍቅር ሲጠመድ
ማልቀስ ይቀናዋል ዕንባ ካይኑ መውረድ

ወላጅ ዘመድ ወዳጅ የሚሞትም ለታ
አንባ አይደለም ወይ ሐዘን የሚገታ

በየምክንያቱ ለሚገጥመን ችግር
በአንባ ከሆነ ሐዘን የሚበገር

ሚስት አግብቶ ሲወልድ የበኩር ልጅ ሲያይ
ደስታውን ሲገልጽ ሲያለቅስ ስናይ

በንዲህ ያል ሁኔታ ደስታ ሲገጥመን
ማልቀሱ ማንባቱ ሸረ ለምን ይሆን

ሚያዝያ 1963 ዓ.ም.

ሕግ

መጥፎ አንዳንሠራ ሕግ ቢያግደንም
ጥሬ ሥራ ብሎ ሊያስገድድ አይችልም

እንዳ ሽረሪት ድር ረቂቅ ውስብስብ
የሕግ አዙሪት ነውና የሚስብ

የሕግን ውሳኔ በደኖ ላይ ብንጥል
ሕግ ላለቲክ ነውና መለጠጥ የሚችል

ከሕግና ፍትሕ አድልዎ ይራቅ
የዳኖ ኹ ችሎት ይወጠር በሔቅ

በፍትሐብሔር በወንጀል ችሎት
ተከሳሽ ተወንጃይ አንዲይቀርብበት

ከሳሽ ተከሳሽን ባሰት አይወንጅል
ጠበቃውም አይቁም ጠብ በቃ ይበል

ፍቅርና ሰላም አንዲኖረው ሕዝብ
ለተግባራችንም ይኑረን አደብ

ጥር 1985 ዓ.ም.

ሰው መውደድ

ከንቱ ውዳሴ ነው ፍሬ አልባ ነገር
ሰው ወዳድኩኝ ማለት በአንደበት ማፍቀር

በእውነት የወደደ ያረቀረ ሰው
ምግብን ለተራበ ውሀን ለጠማው

ለታረዘ ሰው ልብስ
ለታመመውም ፈውስ

ለከፋውም ሳቅን ላዘነው ማጽናናት
ተስፋ ለአጣ ሁሉ እድሉን ማቃናት

ዳግሞም ከኢትዮጵያ ችግር አንዲጠፋ
ሰላም አንዲሰፍን ሕብረት አንዲሰፋ

ለሀገር ለወገን ሌት ተቀን የሠራ
ሰው ወዳድኩኝ ይበል በተግባሩ ይኩራ!

ኅዳር 1969 ዓ.ም.

የባሰ አያምጣ

የሞት ጽዋን ቀምሶ አፈር አስኪለበስ
ከያሬት ዘፍጥረት አስከዛሬ ድረስ

የሚፈጸም ሁሉ የሚደርስ አደጋ
የባሰ አያምጣ እንጅ ምንም አያሰጋ

ጥር 1985 ዓ.ም.

ደግ ሠርቶ...

ሀብት ክብረት ስናገኝ ሲኖረን ሞገስ
በተመቸን ጊዜ ይለናል ደስ ደስ

ችግር ሲመጣብን የ ኑሮ ትግል
መበሳጨትና ባሳብ መብሰልሰል

ኑሮ እንዲህ ከሆነ ሲደላ መፈንጠዝ
ሲቸገሩ ዳግሞ ማዘን ወይ መተከዝ

የእፍዝዝ አዳንግዝ የቅጣጣሽ ኑሮ
ሲመቸ ቀንጣ ቀንጣ ሳይመቸ እርፍ

መሆኑ ካልቀረ ሲኖር በዚች ዓለም
ደግ ሠርቶ መሞትን የመሰለ የለም

ሰኔ 1975 ዓ.ም.

ክፋት

ክፋት ምቀኝነት የሌለው ፍጡር
ለቅናት ለጥፋት የማይከፍት በር

በአጭበርባሪውና በመሰሪ ሰው
እንዲይበካከል ፊት አያሳየው

ጥር 1986 ዓ.ም.

ኑሮዋችን

አስቲ እንመራመር ያገሩ ሰዎች
ከራስ በመጀመር ከግል ምግባሮች
ሌላን ሰው ሳንነቅፍ ዘለን ሳንተች

ምን እንፈልጋለን ምን ምኞት አለን
ሠርተን ለመኖር ወይነስ ሰርቀን
ጉቦ በልተን ይሆን ዳግሞስ ቀምተን

አማራጩ ቢሆን ሌት ተቀን መሥራት
እርስ በርስ ተፋቅሮ መኖር በጎብረት
ኢትዮጵያን አድረጎ በምዴር ላይ ገነት

ሰላምን አግኝተን በኢትዮጵያ ለመኖር
ጠፍቶ ካገራችን መጣላት መቃቃር
ለፍቅር ለሰላም መፍትሔው ይህ ነበር።

ጥቅምት 1984 ዓ.ም.

ቁልምጫ

ሰው ሲያቆላምጥህ
አንድም ሊሸነግልህ
አሊያም ሊጠቅምብህ

መሆኑን ተረዳ
ጎላ አንዳትጎዳ!

ሚያዝያ 1973 ዓ.ም.

የሰው ጊንጦች

ሰውነቷ ቀፍራራ
አግር አጇ የሚያስረራ

ቀስ ብላ ሰውን ጠጋ
በአፍ በጥፍሯ የምትዋጋ

ጊንጥ ጊንጣጊጥ
ነክሳ ደም የምትመጥ

የማትለቅ ከያዘች
መርዛማ ነች

ልክ እንደ ጊንጥ ቀስ ብለው
ዳግ የዋሀ ሰው ተጠግተው

ምላሳቸው መርዛማ
አስተሳሰባቸው ጠማማ

በሰው ሜንታ የሚኖረ የሚበሉ
የሰው ጊንጦች በዓለም አሉ

ይህን መሰል ጊንጣጊንጡ
ልምዱ ነውና ደም መምጠጡ

ጊንጥ ነውና ሰው ይሸ ሸው
ከአጠገቡም አያድርሰው

ግንቦት 1986 ዓ.ም.

ሕይወት

ሕይወት ስንጂምር አልቅሰን መጥተን
ዳግሞም ሕይወት ስታልፍ ሲለቀስልን

ውጣ ውረድ ያለው የሕይወት ጎዳና
መቼ በቀላሉ ተወስቶ ያልቅና

ሕይወት ሲኖርባት ስታስፈነድቅ
ላላወቀባትም መከራ ነች ጭንቅ

ሕይወት እንዴ እንቅልፍ መኖር እንዴ ሕልም
መሆንዋ ካልቀረ በዚች በአፍ ዓለም

የሕይወትን ሚዛን በማስተካከል
እንደምን ቢደረግ መኖር ይቻላል

መዋተት እንዲቀር ሰው በሕይወት ካለ
ሕይወት በሰዎች ልክ በተስተካከለ!

ሚያዝያ 1976 ዓ.ም.

****

ጤናና ልጅነት እያለህ ከሠራህ
በእርጅናህ ጊዜ መጦሪያ እንዲኖርህ

ዘለዓለም የሚኖር መስለህ በመሥራት
ነገ እንደሚሞት ሰው ዛሬን ኑርባት

ሚያዝያ 1976 ዓ.ም.

ጎረቤት እንደ እሳት

ሰው ወዳጁን መምረጥ የሚችል ቢሆንም
ጎረቤት መምረጡ ማዴግቱ አይቀርም

ከጎረቤት መኖር ሔቁ ይህ ከሆነ
ጎረቤትን አምኖ እሱም ከታመነ

ጎረቤትን መጉዳት አራስን መጉዳት
መሆኑን ይረዳል ያውቀዋል በእውነት

ሰውን ካጋጠመው የጎረቤት ጥሪ
ለችግሩ እሚዳርስ ከዘመድ ከእድሩ

ጎረቤትን በክብር በፍቅር መያዝ
ከመጥቀም በስተቀር የለውም መዘዝ

ይህን የተረዳ ምሥጢሩን ያወቀ
የስጋቱ እግረ መቅ ተፈታ ወለቀ

ጎረቤት እንዳሳት ሊጠቅምም ሊጎዳ
የሚችል መሆኑን ሰው በውል ይረዳ

የጎረቤት ኑሮ ዴንቡን ያላወቁ
ጉዳቱ ከጥቅሙ አይባስ ይጠንቀቁ!

ድንገት በአጋጣሚ እሳት እንዴሚፋጅ
ለሰው ጎረቤቱ ካልሆነው የሚበጅ

ከነገር ለመራቅ አጥር ይለያቸው
አስታራቂ ዳኛ እንዲሆንላቸው

መጋቢት 1979 ዓ.ም.

ሁለት አህዮች

ሁለት አህዮች ታሥረው በቱቻ
በሁለት ሜፎች ብቻ ለብቻ
ከምር ሳር አይተው ሆነ ጉትቻ

አንዱ ለቀኙ አንዱ ለግራ
ገመድ መሳሳብ ሁነ ውጠራ
ተመልካቾችን አጋባ ግራ

በግል ምኞት በግል ጉጉት
ከመወጠረ ከመጋተት
አብረው ቢበሉ ምናለበት?

ከሁለት አህዮች የሚተርፍ ሣር
አጠገባቸው ላለ በከምር
ባለ መስማማት መራብ መቸገር?

ዴዴብነት ነው አህያነት
ብሎ የሚያስብ ካለ በእውነት
ብዙ ይማራል ከዚህ ትዝብት

ግንቦት 1986 ዓ.ም.

ግምበኛና መምህር

ገንቢ የሠራው ቤት ውብቱ ሲደነቅ
አስክ አመድህረ ዓለም የማይነታነቅ

አይፈርስ አይናጋ ይኖራል ዘለዓለም
ተብሎ ሲወራ የሚበልጠው የለም

አስተማሪ ዳግም መገንባት ጀመረ
አያንዳንዱቷን ቃል ጠንቅቆ አያኖረ

የማይታይ ሁኖ በእጅ የማይደሰስ
የመምህሩን ሥራ ሁሉ ሰው ሲያንኳስስ

መምህረ ያነጸው የወጣቱ ዕውቀት
ድንቅርናን ንደ አያለ በሕይወት

ገምቢው የሠራው ቤት ከሥር መሠረቱ
ነፋስ ገነጣጥሎት ወጣ አንኩትኩቱ

ሚያዝያ 1944 ዓ.ም.

ውሸት

ውሸት ደቦ ቢሆን ረሀብ ባልኖረ
ውሸት ልብስ ቢሆን ስንቱ ላይ ባማረ

ውሸት ጥበብ ቢሆን ስንቱ በተካነ
ውሸት ኪነት ቢሆን ስንቱ በዘረነ

ውሸት ዕውቀት ቢሆን ስንቱ በተማረ
ውሸት ግን ውሸት ነው ዘበት ሁኖ ቀረ

ግን አንዳንድ ሰዎች ውሸት የሚወዱ
ለውሸት ተገዝተው ለውሸት ያበዱ

በውሸታቸው ልከ ጥርሳቸው ቢወልቅ
የስንቱ ድድ ነበር ፀሐይ የሚሞቅ?

ውሸታም ነው ብሎ ሰው እንዳይሸሸው
ሰው ነኝ የሚል ሁሉ ውሸትን ይጥላው

ሰው በውሸት ዓለም መንሸርሸረን ትቶ
ይኑር በሐገረ በዕውነት ተጨምቶ

ሐምሌ 1976 ዓ.ም.

ቤት አፍራሽ

ሰዎች ተሰብስበው በግንድ ሲነርቱ
ያንዱን ቤት ገጽታ በሆታ ሲመቱ

በጥቂት ዳቂታ ወዲያው ከመቅጽበት
ተንኮታኩቶ ቢወድቅ ያ የደራ ቤት

ያን መሳይ አዳራሽ የሚያፈርሱ ሰዎች
አፍራሽ ብቻ ናቸው ወይ ጭምር ገንቢዎች?

ብዬ ብጠይቀው ዋናውን መሐንዲስ
ይህን መለሰልኝ ይባስ ብሎ ይብስ

እዚህ ቦታ ያሉ ሁሉም አፍራሽ ናቸው
ከዚህ የተሻለ ዕውቀትም የላቸው

ማፍረስ ማፈራረስ ዳግሞም ማፈራረስ
ጥበብ ችሎታቸው የለም ከዚያ መለስ

ዳሞስ ቤት ለማፍረስ ምን ዕውቀት ያሻዋል
ሺ ዓመት የገነቡት ባንድ ቀን ይናዳል

ብሎ የሰጠኝ መልስ እጅግ አስደንቆኝ
እኔስ የማን ወገን የትኛው ጎራ ነኝ

ብዬ ሳሰላስል እራሴን ስጠይቅ
ለጥያቄዬ መልስ ስፈልግ ስጠብቅ

ለማፍረስ ለማጥፋት ከማባከን ጉልበት
እንዲያው በደፈናው ይሻላል መገንባት

የሚል መልስ ሳገኝ መንፈሴ ቢረካ
አልኩኝ በሀሳቤ ይሽም አለ ለካ!

ሐምሌ 1985 ዓ.ም.

ለምን?...

(ቅኔያዊ ግጥም)

የሰው ነገር የሰው ሕልም
ታልሞ አያልቅም ተወግቶም

ደባ ሠሪ ደመኞችን
አዛዥ ቢኖር አጋችችን

እፍን አግድ ቢቀር
ለምን የሚል ባለነበር

መላ ያጡ ሰበብ
ዋናቸው የሃሳብ

ይሽን መሰል ጥሬ መላ
አረገ ወይ ወደ ሌላ

መች ተነሳ እውነተኛ
ዘር አዳኙ ጉልበተኛ

ይልቅ ፈልግ የተሻለ
ቀርጦ ጠጋኝ እንዳለ

ጉድ ባይ ሲሉ ዛሬ መጥተው
ባጉል ስለት አመሃኝተው

ላያዛልቅ አጉል ስለት
መለማመጥ ላይቀርጥለት

ወግን ውደድ የሚያስቅ
ለምን ብሎህ ከምትበሽቅ

1985 ዓ.ም.

ሠርቶ መወቀስ

ለሕፃናት መልካም ዕድገት
ለሕብረተሰብ ጤንነት
ሁሉን አሟልቶ ማዘጋጀት

አንዱ አጠፋሁ ተቆጥሮ
በመሃይምናን በደንቆሮ
በማይችል አንገት አዙሮ

ተነዛና አሉባልታ
በመመስገንም ፈንታ
በባለሥልጣን ልንገላታ?

ወይ ዘመን፣ ዘመነ ተገላቢጦሽ
ጉልበት ሀብቱን የሰዋ ተወቃሽ!
የባለገ ባለ ሥልጣን ተወዳሽ!

ዶክሞ ሠርቶ መስጠት
በዚያም መመስገን መርካት
ተነፍጎኝ መጉላላት?

በ ኔ ላይ ግፍ የደረሰው
የ ኔ ካሣ ዳርግ ሁኖ ነው?
ወይስ አሪ በክንቱ አሪ በክንቱ ቢሆን ነው?



ጎብረት አፀደ ሕፃናት በኢንጅነር ታደለ ብጡል ከብረት ግንባታ ተሠርቶ ለከፍተኛ 14 ቀበሌ 12 ሐምሌ 1976 ዓ.ም

የጠረጴዛ ኳስ ጨዋታ

የጠረጴዛ ኳስ ጨዋታ
ቅው ቅው ታ፡- ታ ታ

ወደ ቀኝና ወደ ግራ
የዓይን ጅው ጅው የአንገት ሥራ

መረብ ሲያግዱት መረት ስትነካ
አንዱ ሲያዝን ሌላው ሲረካ

ቁጭ ብድግ መቁነጥነጥ
ወይ ማጨብጨብ አለያም ጸጥ

ቂ ወደ ግራ ቂ ወደ ቀኝ
የኳስ ፈንጣ የኳስ ትንኝ



ጠረጴዛ ላይ ጨሀ ዘልላ
ያንዱ ቁጥር ዛያ ሲሞላ

በቂፍ ያለው ተመልካች
ከንፈር ሊመጥ ወይ ሊተች

ኳስ ነጥራ መረት ስትወድቅ
አኮብኩቦ ሲጠባበቅ

ቁጥሬ ሃያ አንድ ሲሞላ
የተሸናፊ ደም ሲፈላ

ተመልካች ሲዋልል
ግራና ቀኝ ይታያል

ቁጫጭ ኪስን ለጠነጋው
ሲያጨበጭብ ላሸናፊው

ቅው ቅው ታ- ታታ
ጸጥ ይልና ለአንዲፍታ

ዳግሞ ሌላ አዲስ ቡድን
ይጀምራል ጨዋታውን

ግራ ማየት ቀኝ መዘር
የአንገት ዝው ዝው ሲጀመር

ቅው ቅው ታ- ታታ
መጫወት ነው ጣትም- ማታ

ጥቅምት 1973 ዓ/ም

ማዕድንህን ቅበር

ወርቅ ማዕድንህን ለፈረንጅ ሳትሸጥ
አጥፍ ካስከፈለህ ለቆርኬ ልብጥ

አትሸጥ አትግዛ ከየካፒታሊስት
በቁምህ ደምህን ከሚመጠምጡት

የአገርህን ፍሬ በያይነቱ ገዝቶ
ካልከፈለህ ላንተ ዋጋው ተገምቶ

ይቅር ባታመርት ብለህ ለገበያ
ለአትራፊ ነጋዴ አንዳትሆን መዋያ

ድንጋይ ፈልጠህ ፈልጠህ እጅህ እስኪነታ
የሚሰጥህ ደሞዝ ለ ኑሮህ ካልበቃ

ይቅር ባይሠራ ሰማይ ጠቀስ ቤት
መኖርያ ለነሙቾ ለነመኳንንት

ተምረህ ካልሠራህ ለአገር ለወገን
መበላለጥ ቀርቶ አቻ ለመሆን

መሃይም ሁነና ወገኑን አፍቃሪ
ተባል ቆራጥ ጀግና መብት አስከባሪ

1956 ዓ/ም

ሰላም ለዝክረ

ሰላም ለአገረ ልጆች አረቅም ይሁን ቅርብ ያላችሁ
የፍርድ ገምድልን ሁኔታ አስቲግ ላውጋችሁ

ጧት በማለዳ ወደ አንድ ፍርድ ቤት ሄጄ
የሰማሁት አበሳጭቶኝ ተመለስኩኝ ተናድጄ

ሰላም ለአሳዛኙ በስርቆሽ ለተከሰሰከው ጉብል
ለትምህርት ዕድል ያልኖረው ሥራና ልብስ መብል

ፍርድ ቤት ቀርቦ በአቃቤ ሕግ ተከሶ
ተመሰከረበት መሥረቁ ጥቂት ዱቄት የበሶ

ሰላም ለአቃቤ ሕጉ ፍርድ አንዳይጓደል ጠባቂ
የስርቆትን ወንጀል መቀመን በጣም አጣርቶ አዋቂ

በመጠየቁ አንዲቀጣ በአንድ ዓመት አሥራት
ወጣት አንደሆን መቀጣጫ የተራብ አንዳይሰርቅ ለራት

ሰላም ለዳኛው ከፍርድ ሰሞ ያለ አድልዎ
ሕግ አዋቂ ረኅራህ ነፍት ልበልዎ?

ሥራ አጥቶ ተገዋላይ ተርቦ የሰረቀ
በአስር ቤት ሆኖ በበሽታ ከማቀቀ

ሰላም ለአንባቢዎች አግዚአብሔር ያሳያችሁ
አንድ የመንደር ዳኛ ተከሰው እዚሁ ፍርድ ቤት ቀረቡላችሁ

የተከሰሱበት ወንጀል ጉቦ በመቀበል ስለነበረ
ይሽውም ተነጣጥሮ በብዙ ሰዎች ተመሰከረ

ሰላም አሁንም ለቀድሞው ሕግ አስከባሪ
ፍርድ አንዳይጓደል በሕዝብ ስም ተከራካሪ

በቂ ደሞዝ ያላቸው ላይቸገሩ ጉቦ ከበሉ
ብለው ጠየቁ ይገባል አምስት ብር ይቀጣሉ

ሰላም አንዲሁም ለቀድሞ ፍርድ አስተካካይ ዳኛ
ሕግ አዋቂ ትልቅ ሰው ስለነበረ ሁነኛ

የተከሳሹ ዳኛ የመጀመሪያ ጥፋታቸው በመሆኑ
በማስጠንቀቂያ ብቻ በነፃ አንዲለቀቁ በየኑ

ሰላም ጉድ ለሞላብሽ አገር
የራበው ሲሰርቅ ሲታሰር

የሞላው ነጥቆ ሲንበሸበሽ
ከቶ ምን ይሆን መደምደሚያሽ

ሰላም፣ ሰላም - አንደይደጋገም ወንጀሉ
ሸረ በዳዮችን አንድበሉ!

1965 ዓ/ም

ሜማ ጠራጊ

በየአደባባዩ በየጉራንጉረ
ቀለም ብራሽ ሰንዴቅ ይዘው የሚዞረ
ሜማ በመፈተግ ደክመው የሚኖረ
አሉ ብዙ ልጆች ምንም ያልተማሩ



በሌሊት ተነስተው መንገድ አየዋለ
በጥናትም ፋንታ ቢሳ እያቃጨሉ
ይህ ቀለም መግዣ ይህ ለምሳ እያሉ
ላባቸውን ጠርገው ደክመው ይበላሉ

ባዶ እግር ቢሄዱ ቡትቶ ቢለብሱ
ሜማ ላይ ቢወድቁ በጣም ዝቅ ብለው
ባይደርስ ነው እንጂ ለነሱም ዕጣው
አይደለም በማነስ ከባለፀጋው

ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማሪነቱ
አግር አጥቦ አንድ ጊዜ ለዓለም ማሳየቱ
ለሰው ልጅ መሆኑን ትህትና ሀብቱ
ነው እንድንረዳው ይህን ማምቱ

ቡትቷም መሃይም ብሎ ከመናቅ
ሜማ ጠራጊ ነው ብሎ ከማራቅ
በሰንካላ ዕድሉ በሰው ለመሳቅ
ነግህ በኔ መሆኑን ይገባል ማወቅ

መስከረም 1942 ዓ.ም

መዋሸክ

ምን ያለ ዘመን ነው ዘመነ ብልሹ
መዋሸት ብቻ ነው ትልቁም ትንሹ

ባገራችን ባሕል በአገራችን ልምድ
አስነዋሪ ነበር መዋሸክ መልመድ

ግን የዘመኑ ሰው ልማድ ያደረገው
ትንሹም ትልቁም ሰውን ማማትን ነው

ለዚች ላጭር ዕድሜ መቶ ለማትሞላ
አንዴት ሰው ይኖራል ሰውን እያጣላ?

የመዋሸክና የሐሜት ዘይቤ
ለያስፈልግኝም ይራቅ ካጠገቤ
ብሎ የሚል ወጣት ወይም አረጋዊ
ምነዋ በኖረ በሔቅ ኢትዮጵያዊ

1959 ዓ/ም

ደሮ ጨሽት

ደሮ ኩኩሉ ሲል ሊነግር መንጋቱን
ድምፁ አስታውሱ ይላል የተረላውን
የልጅነት ጊዜን ዳግሞም የርጅናን
ቤትን ጎረቤትን እንዲሁም ሥራን

ዳስታና ሃዘን ይፈራረቃሉ
ምቾትም ከሞንቅ ጋር ይለዋወጣሉ
የደሮኹን ጨሽት ፍፁም ይረሳሉ
አሉ ማለት ቀርቶ ሞቱ ይባላሉ

ይህ ነው የኔም እጣ በሞትኩኝ ጊዜያት
ደሮው መጮሽ አይተው ሌሊቱም መንጋት
ታድያ ምን ያደርጋል የጨሽቱ ብዛት
አልሰማው አላየው አኔ የለሁበት

1959 ዓ/ም

****

የሚያውቁትን ሁሉ መናገር
ያዩትን ሁሉ መመስከር

ያገኙትን መብላት
የሰሙትን ማውራት

ሁሉ በሙሉ አይታመን
ሁሉ ለሁሉም አይሆን

በሰላም ይዴጉ

ጋራና ሸለቆው እንዲሁም በረሀ
ሐይቅና ውቅያኖስ ዳግሞም የወንዝ ውሀ

ሰማይና ሕዋው ሰው አልባ ጠፈር
ከዋክብት ጨረቃ ፀሐይም ሳትቀር

ዳመናና ዝናብ መብረቅና ንፋስ
ሲፈራረቁባት አርጅታ አማትኩስስ

ዓለማችን የእኛ መረት የምንላት
ስንት በጠቀመችን እኛ ካወቅንበት

ሰፊ ናት ሰፊ ናት ምድሪቷ ዓለም
አትክልትና አዝርዕት አፍሪ ነች ለምለም

የምታፈራውን ብንበላ ብንቀምስ
ንጹሁን አየርዋን ምገን ብንተነፍስ

ጋራ ሸንተረሩን በረሃና ጫካ
ተንሸርሸረንበት በመንፈስ ብንረካ

ዓለም ጤና ነበር ሀገርም ሰላም
እንዲያው ባይበክል በኒውትሮን በአቶም

ሰላም እንዲሰፍን በዓለም በሙሉ
የኒውትሮን የአቶም ጦር መሣርያ ሁሉ

ይበታተንና ብረቱ ይቅለጥ
ለእርሻ መሣርያነት ቶሎ ይለወጥ

መሬቱም ይታረስ ያፍራ እጥፍ ድርብ
ችግር እንዲወገድ እንዳይራብ ሕዝብ

ልጆቻችን ሁሉ በሰላም ይዴጉ
ይኑሩ ይማሩ በዕውቀት ይመንዴጉ

1959 ዓ/ም

ይገርማል

የሰው ልጅ በለቅሶ መወለዱን ማብሰር
እያደገ ሲሔድ በቋንቋ መናገር

ከዚያም በዕድሜው ጉዞ ውጣና ውረድ
ሲመላለስበት ወልዶ ሲዋለድ

ከቆየ በኋላ ለውስን ዘመናት
ጸጥ በሚልበት ቀን በለቅሶ መ ሸ ኘ ት

ገሀድ ሁኖ ሳለ ይህን መሰል ዕጣ
መጪነቅ መጠበብ ምን ፋይዳ ሊያመጣ

ለገንዘብ ሲገዛ ተስገብግቦ ሲኖር
በጣም ያሳዝናል ሰው የሚባል ፍጡር

ዋ ሽ ቶ ተስገብግቦ በዓለም መኖሪ
በጣም ይገርመ ኛ ል ከቶ አለማፈሪ

ስለዚህ ፍጡራን የሰው ልጆች ሁሉ
ደግ ዳጉን ጎደና ይምረጡ በመ ሉ

1983 ዓ/ም

ሲቺሊያዊ ሀብታም

ከሲሲልያ ዳሴት ከጣልያን አገር
ተሰዶ የሔደ አሜሪካ አሜኖር

ብዙ ተግቶ ሠርቶ አከማችቶ ሀብት
አላፊ አግዳሚው አስኪቀናበት

ከንግድ ድርጅቶች ፋብሪካዎች ጭምር
ሀብቱ ተገመተ ብዙ ሚሊዮን ብር

ያውም ወደ አገሩ ለዘመድ የላከው
ለበጎ አድራጉትም ወደ የለገሠው

የሠራው መዝየም ዳግሞም ሌላ ሌላ
ከሂሳቡ አልገባም አብሮም አልተሰላ

መ ቸም ፍጡር ሁኖ አንድ ቀን መሞት
የማይቀረው ዕዳ መሞቱ በድንገት

በሕመም አስታክኮ እጅ እግሩን ጨምሮ
አንዲይናገርም አፍ ምላሱን አሥሮ

በአልጋ ቁራ ኛ ነት ቢተ ኛ ሐኪም ቤት
ወረው ተናፈሰ ሀብታሙ አንዲሚሞት

ሴት ወንድ ሳይበሉ ያሉት ዝርያዎች
ከአሜሪካን አገር ከኢጣልያ መንደሮች

ወረውን የሰመ ዘመዶቹ ሁሉ
ከያሉበት አገር ሰልክ ደዋወሉ

ኑዛዜ ፍሊጋ እሱ እያለ በነፍስ
ተጠራርተው መጡ ሐኪም ቤቱ ድረስ

የዘመድ የአዝማድ ግርግር ሁካታ
መድኃኒት ሆኖ ደምሥሮቹ ሠረ ምላሱም ተረታ

መሞቱ ቀረና አስከናካቴው
ጤናማ መሆኑን ሐኪም ቢነግረው

ዘመዶቹ ሙሁ በጣም ደነገጡ
የሀብት ክፍያው ዕድል በማምለጡ

ከዘመድ ጥርቅም ወራሽ ነን ከሚሉ
አውራሽ ከሞት ድኖ ሲጫወት ከሁሉ

ከመሐከላቸው ሰባት ዘመዶቹ
የሚሞትበትን ዘዴ አመቻቹ

እሱ በመዳኑ የደስ ደስ ነው ብለን
ምግብና መጠጥ ዳንኪራ አዘጋጅተን

እንጋብዘውና ከሰሞኑ ማታ
እዝያው እንግዳለው በጥይት እረምታ

ብለው ሲማከሩ ሰምተው ሠራተኞቹ
እንዳገና ታመው ይተኙና ጌቶች

የዘመድም ይሁን ወይም የወዳጅ
ግብዣ ነው ተብሎ ድግስ ቢዘጋጅ

አዳራ እንዳይሔዱ ይስጡን ቃልዎን
አሽከሮች ሰለሆኑ አይናቁት ምክሬን

ብለው ቢማጸኑት ለምን ይሆን ብሎ
ጉዳዮን አጣሪ ጥቂት ሰው መልምሎ

ጠያቂ ዘመዶች ቢያሉበት ቦታ
የሚደል ቱትን ወይም አሉባልታ

አጣርታችሁ አምጡ ብሎ አንዲሠማራ
ሰባት ዘመዶቹ ከማፍያ ጋራ

በውርስ ከሚያገኙት ገንዘብ ለማካፈል
መስማማታቸው ሀብታሙን ለመግደል

የሰባቱንም ስም ከነአባታቸው
ያገዳደሉን ስልት ተልመን ጨምረው

አለትና ቀኑን ቦታውን ጭምር
አጣርተው አመጡ ከነምስክር

የዘመዶቹን ጉድ አየደረደረ
ሀብታሙም ሰውዬ ፖሊስ አማከረ

ፖሊሶቹም አሉ አንተ ጥራን አንጅ
እነሱን መያዙ ምንም ጊዜ አይፈጅ

በዚህ ተመካክረው ጨርሰው አንዳለ
ሀብታሙ ዘዴውን ፍሊጋ ቀጠለ

ብልጭ ብሎ ታየው አንድ ደህና መላ
ይህም ግብዣ ማድረግ ለዘመዱ ሁላ

ነበረና ዘዴው ለሱ የታየው
ድግሱን ዳገሰ አንደመሰለው

ግን ከዚያ በፊት ብዙ ሚሊዮን
አሳትሞ ኑሮ የውሸት ብራን

ዘመዶቹን ሁሉ 2,000 ሰው
ለግብዣው ጠራቸው እሱ እንዳቀደው

ሲበላ ሲጠጣ ሳቅ ጨዋታው ደምቋል
የግብዣውም ጥሪ ለፖሊሶች ደርሷል

ሞቅ ያለውን ግብዣ ለማድመቅ በይበልጥ
ተጋባዥዎቹን ሲሰም ሲጨባበጥ

ከቆየ በኋላ አጨብጭቦ እጁን
ብራን አምጡ ብሎ አዘዘ አሽከሩን

በሣጥን በሣጥን የታጨቁ ብሮች
የመቶና የሺ ሁ አዳዲሶች ኖቶች

ተከፍተው ሲታዩ ተጋባዥ ዳሰ አለው
በሕይወቱ አያለ ሊያከፋፍል ነው

ብለው ሲወያዩ ኑ አዳጅ አንውጣ
አንግዳና ብራም ሁሉም አብሮ ይውጣ

ብሎ አዘዘና እሱ አየቀደመ
ተጋባዡ ሁሉ ወደውጭ ተመመ

ተዘጋጅቶ ኑሮ ቤንዚንና ክብሪት
ብራ ላይ አፍስሶ አጋየው በእሳት!

ወገኖቼ አንግዲህ ብራ ተቃጠለ
ምን ትወርሱ ይሆን ከዚህ ሌላ የለ?

አለና ሲናገር አንግዶቹ ሁሉ
ወዳየመጡበት መሔድ ሲጀምሉ

አስቲ ቆዩ አንዳፍታ! ምሥጢር ልንገራችሁ
አገሌ አገሌ ወዲህ ኑ አባካችሁ

ብሎ አስጠራና ሰባቱንም ሰዎች
እነዚህ እኒው ዘንድ ያዳኑ ዘመዶች

ሊገድሉኝ አስበው ለገነዘቤ ጌጉተው
መማከራቸውን ሠራተኞች ሰምተው

ሰላስጠነቀቁኝ ከአደጋው በፊት
ያጌጌችውን ብር ነው ያቃጠልኩት

ተአንግዲህ ይወቀው ወዳጅም ዘመድ
ብራ አንዲሁ ተቃጥሏል ሁኗል ዶግ አመድ

ብሎ አንደጨረሰ ተናግሮ ሀብታሙ
ሰባቱንም ሰዎች ፖሊሶች ለቀሙ!

ጥቅምት 1986 ዓ.ም

****

የወራሾች ለቅሶ ግማሽ ሳቅ መሆኑ
ከአንባቸው ዘለላ ይታያል በአውኑ!

አንጀባ

በዕውቀቴ ግን ተሰተካክሎኝ
በሥራዬ ገናና ነኝ
ነው አንጀ ጊዜ ጥሎኝ
ይሽ ይሽ በነበረኝ

ይሽን ፈለሰፍኩ ይሽን ሠራሁ
አያልኩ ባፈ ብዙ አወራሁ
በተግባር ግን መቼ አሳየሁ
ለቁም ነገር መቼ በቃሁ

ያለ ተግባር ወሬ በማውራት
በመመጻደቅ ወይ በመኩራራት
አለመብቃቴን ለሰውነት
ይሽው ተረዳሁ በእውነት

ግንቦት 1986 ዓም

ምዕራፍ ፱

ፍቅር



ሕፃን ቴዎድሮስ ታደለ ብጡል ክብረት

ምዕራፍ ፪

ፍቅር

ኮረዳ	63
ትዝታ	65
ናፍቆት	66
የኛ አካል መጉዳል	67
አንቺን አይጠጋ	69
ጥምባ አሆ	69
ፍቅር ወረተኛ	70
በፍቅር ሽ አልጨት	71
ወድቂ ተሰበርኩ	72
ስልክ ተደወለ	73
ሐዘኔ ከበደ	74
አልቻልኩም አብሮ መሰዳድ	75
ታማሁኝ በፍቅር	76
የቆሰለው ልቤ	76
በል ክብርዋን መልስ	77

ኮረዳ

መልኳ ጠየም ያለ ፊቷ የረቀቀ
አንገቷ ብርሌ ዳሌዋ የላቀ

ጉንጮቿ የፈኩ የመሰሉ እንኮይ
ዓይኖቿ ገራፊ ከረቅ ሰውን ጣይ

ቅንድቦቿ መሳይ የተከረከመ
ሽፋሽፍቷ ረጅም ሰው የሚያስገርመ

ከንፈሮቿ ለጋ ሳመኝ ስመኝ ባይ
ፀጉሯ አረፍ ያለ ከወገቧ ላይ

ከንፈሯ ሲገለጥ ለመሳቅ አንድስፍታ
የጥርሷ ንጣቱ ምኞ የሚያስመታ

አጉጠ ጉጢዋ መሳይ የባህር ቅል
ሰው የማያስጠጋ ገፍትሮ የሚጥል

ባቷን ተረከዟ ወገቧን ጭምር
ፈጥሮታል ፈጣሪ ምንም ሳያስቀር

በአንዲህ ያለ ውበት ወጣቱ ተነድፎ
ማሰብም አልቻለ ቀረ ተዝለፍልፎ

ዓመሏን ሞያዋን መርምሮ ሳያውቅ
ላግባሽ አግቢኝ ብሎ ሄዶ ሊጠይቅ

እሱም በክፉ ሽጋ በመሆኑ
ወዶድኩህ አለችው እዚያው ወዲያው ኑ

ታጥቦ የማይጠግ መሆኑን ቁንጅና
ያወቁም አይመስሉም የሰመ በዝና

ሳይተዋወቁ እንዲያው በችኮላ
ተጋቡ ሰሞኑን ቃል ኪዳን ተሞላ

ወርም አልሞላቸው እውነቱን ሲረዱ
ትዳር በቁንጅና ብቻ አለመሄዱ

ጎላ እንደሰማሁት ሰው እንዳነገረኝ
ትዳራቸው ፈርሶ ተፋቱ ብሎ አለኝ

ሳይመራመሩ አግብቶ ከመፍታት
ይሻላል መላመድ ነገሩን ማጣራት

ባሉብ በሔሊና ዳማም በመንፈስ
ያሻል መገባባቱ እስከሞት ድረስ

1950 ዓ/ም

ትዝታ

ወዳሽኝ ወድጄሽ ትዳር መሥርተን
ከአኖ አብራክ የወጡ ልጆች አፍርተን
ሰላምና ፍቅር እየተጉናጸፍን
በደራው ቤታችን በምቾት ኑረን

የአኖን ኑሮ ማማር የምቾት ሁኔታ
አያዩ የቀኑ ነዝተው አሉባልታ
በትዳራችን ውስጥ በነዙት ሐሜታ
አጉል ተበጣብጠን ዳረስን ልንፋታ

ዳስ ብሎን የኖርነው በሳቅ በጨዋታ
አይዋሽ አይነቅዝ ያለፈው ትዝታ
የሰው ወረ ንቀን የሰውን ሐሜታ
በሰላም አንኑር በፈጠረሽ ጌታ

ዕጣችን ከሆነ ተለያይተን መኖር
ላንቺም ለኔ ዳስታ ለልጆቹ ክብር
ትዝ ይበለንና የኖርነው በፍቅር
እንድንጠያየቅ መ ኩራረፍ ይቅር

1972 ዓ/ም

ናፍቆት

መለሎ ቁመናሽ ቀጭን ወገብሽ
ኮራ ያለ ዳሌሽ ጉች ጉች ጡትሽ
ሸረ አንዴት ከረመ አንችስ ደህና ነሽ?

እኔ በከሌ በጣም ደህና ነኝ
ግን ለደብዳቤ ዮ መልስ ሳላገኝ
ባንቺ ናፍቆት ብቻ ሞቼ እንዳትቀብሪኝ

ቢሮ ዮ ስገባ ሰብስባ ስቀመጥ
አሳቤ ኩብሎ ወደንቺ ዘንድ ሲሮጥ
ሥጋቴ በዛና ጀመርኩኝ መዳንገጥ

በሰው በደብዳቤ የላክሁት መልዕክት
ዳርሶሽ ነው ዝም ያልሽው ወይስ ረሱት
እኔ እምሰቃየው በዝናሽ መጥፋት

ክፋም ተናግሬሽ በነገር መሐል
አስቀይሜሽ ከሆንኩ ፈጽሜ በደል
ባይሆን ለይቅርታሽ ካሳውን ልክፈል

ይቅር ግድ የለኝም ያለፈውስ ይለፍ
በሽታ አንዲይዘኝ አብጄ አንዲልከንጭ
ለዚች ለደብዳቤ ቶሎ መልስሽ ይጻፍ

ጎደር 1970 ዓ/ም

የኛ አካል መጉደል

እኔ እንደምወዳት አሷም የምትወደኝ
ለጋስ ልበ ሩሕሩህ እሙኛ ነበረኝ

በፍቅር ሠረገላ አኛ ስንጋልብ
ያየና የሰማ ጀምሮ መንገብገብ

አሷ ዓይነ ሽውራራ እሱ አግረ ወልቃማ
አሷ ለምቦጫም ነች የሱ አፍ ጠማማ

ይሽን በመሰለ ዳግሞም ሌላ ሌላ
ሲያሙና ሲሰድቡን አኛ እንድንጣላ

ጀሮ ደባ ልበስ አንሰማም ብለን
ጥቂትም ሳንቆይ ጋብቻ ፈጸምን

ከዚያም ሰዎች አሉ ይሽ ጋብቻ ቸው
ነገውን ሊፋቱ ከቶ ምን ፋይዳ አለው!

አንኳን ልንፋታ ፍቅራችን ጠናና
የልጅ ጸጋ አንድናይ መጣ አርግዝና

አሁን አሷ አርግዛ የሚወልዱት ልጅ
ጠንጋራ ፎናና አግር የሌለው አጅ

አይቀረ መሆ ኑን እንዳምን አያው ቁም
ይልቅስ ከአ ሁ ኑ ማጪንገፍ አይበጅም?

በመፋቀራ ችን ሰም ች ሁ ሉ ቀንተው
ብለው ሲሳለቁ በ ኛ ኑሮ ገብተው

ጪናማ፣ ጠንካራ አምስት ልጆ ች ወልዴን
ይመስገን ፈጣሪ የልጅ ልጆ ች አየን

ሚስቴ ዓይነ ሽ ውራ ራ አ ኔ እግረ ወልቃማ
እሷ ለምቦጫም ነ ች የ ኔም አፍ ጠማማ

የ ኛ አካል መ ጉዳል ሲላ ሰው አይ ጉዲ
የሔሜት ጋጋታ አይኖረውም ፋይዳ

****

ስለዚህ የሰው ልጅ በሰው ኑሮ ገብቶ
ሔሜት ከመዘባበብ እንዲያው ሥራ ፈትቶ

በሰው ሕይወት ገብቶ የሚፈተፍት
ምነዋ <u>በታ ኘው</u> የራ ሱን ሕይወት

1969 ዓ/ም

<u>አን ቺን አይጠጋ</u>

ያን ጉራ ጉር ሽ ል ኝ በመረዋ ድም ጽ ሽ
ሲያውዱ ኝ የነበረ ያ ሽ ቶ ጠረን ሽ
ትራስ የነበረ ኝ መክዳ ጡቶ ች ሽ
እማ ኝ አንዲሆ ኑ ኝ ላድርጋ ቸው ነቃ ሽ

በዕውነት ላፈቀረ ት መሆን መስዋዕት
የቆየ ነውና ከአያ ት ቅመ አያ ት
በወረ ት መዳሰ ት አስኪያልፍ ወረ ት
ም ኖ ት ሽ መሆ ኑን አ ሁን አወቅ ሁ ት

ሕይወቴን አጋልጠ ሽ ለሕመም ለአደጋ
ፍቅረን ቸል ብለ ሽ ከሔድ ሽ አሌላጋ
የ ኔውስ የ ኔነው ምንም አያሰጋ
ብ ም የ ኔ ሐዘን አን ቺን አይጠጋ

1950 ዓ/ም

<u>ጥምባ አሆ</u>

ባማር ኛ ቋንቋ ጥምብ አሆ የሚሏ ት
የሲጋራ ቅጠል ሰም ች የሚያጨሷ ት
አጭሶ አጭሶ በጭስ መታፈን
ለደስታ? ለሕመም? የት ኛ ው ይሆን?
አውነ ትማ ባይሆን ባያስደስትማ
መ ች ሰው ያጨስ ነበረ አፋ አንዲገማ?

1949 ዓ/ም

ፍቅር ወረተኛ

ፍቅር እንደሞት ጥላ በድን አደረገኝ
አጥንቴን ሰብረው ኩቶ አዝለፈለፈኝ
ፍቅር በአበባው መዓዛው ጣፈጠ ኝ
አሁን ግን ጠውልጉ ሽታው አሰለቸ ኝ

የፍቅር ክፋቱ ትዝታ ነው ሲሉ
አላመንኩም ነበር ውሸት በመምሰሉ
አሁን ግን አወቅሁት ይሰማኛል ቁስሉ
የነደፈኝ መርዙ የወጋኝ ኮተሉ

ይህ ጣፋጭ እንደማር መራር እንደኮሶ
ልፍስፍስ እንደጥጥ ጥብቅ ከምሰሶ
ዛሬ ህይወት አለው ነገ ይቀራል ፈርሶ
ፍቅርን አትመኑት ቢታይ ድርብ ለብሶ

ጥር 1945 ዓ.ም.

በፍቅር ሽ አልሞት

ከልቤ ማፍቀሬን ተናግሬ ሽ በአፈ
ይህኑ ለማብሰር በእጄ ቼ አቀፈ

ከንፈሬ ከንፈር ሽን የመጥኝ አያለ
ዓይኔ ሲስለመለም ሰውነቴ ጋለ

ጋለ ሰውነቴ ልቤ አለ ድውድው
ምን እንዳነካኝም ም ኑንም ሳላውቀው

ሰውነቴን ስቼ መውደቅ ተዝለፍልፈ
የጣሙን የቆጡን እንዲህ መለፍለፈ

እብዴት ነው ጤንነት እንዲህ ያለ ነገር
ወይስ ማብሰሬ ነው ላንቸ ያለኝን ፍቅር

እንኮይ ከንፈርቸ ሽ
ዛጉሎቸ ዓይኖቸ ሽ

ክፍት ክድን ሲሉ ለጥቅሻ ለሳቅ
ነጉላ አደረጉኝ ምንም የማላውቅ

የቀሞኔ ጸጉር ሽ ሎሚ ተረከዝ
ተገትሬ እንድቀር አረጉኝ ፍዝዝ

መለየት አቅቶኝ ካንቺ ራቅ ብዮ
ጥላ ሽን ስከተል ሳላገኝ ሽ ውዮ

ስበር አልነበረም ታዛቢ እንዲሚለው
በገዛማ ጣቴ ዓይኔ ሊወጣ ነው

አካል ሽ በሙሉ ሆነብኝ መተት
ሸረሪ አንድ በይኝ በፍቅር ሽ አልሞት!

1980 ዓ.ም.

ወድቂ ተሰበር ኩ...

አተኩሮ ሲያየኝ ቀዝቃዛ መሰል ኩት
አፈፍ ቢያረገኝ እጁን ቀዘቀዝ ኩት

ሽንጤን ጨበጥ አርጌ አንገቴን አቅንቶ
ዓይን ዓይ ኔን እያየ አፍ ከንፈሬን ከፍቶ

ሳም-ላስ ቢያደርገኝ ዕውነት ቀዝቃዛ ነኝ
የሱ ከንፈር መሞቅ እኔን ግን ገረመኝ

ከዚህማ ወዲያ ምኑ ይጠየቃል
ቃናዬ ተስማምቶት ምራቄን ይውጣል

ዳጋግሞ ሲስመኝ ሲመጠኝ ሲልሰኝ
ሰውነቴ ሲቀል አቅም ሳጣ ተሰማኝ

ፍላጌት ምኖ ኩ ሞልቶለት ሲረካ
ገልበጥ ቀና አድርጎ ገላዬን ሲነካ

ድንገት ሳያስበው ግፍትር ሲያደርገኝ
ወድቂ ተሰበር ኩ የመጠጥ ጠርሙስ ነኝ

ጥር 1984 ዓ.ም

ስልክ ተደወለ

ስልክ ተደወለ
መላልሶ አቃጨለ

እኔ አነሳሞለሁ ብላ ርጠቸ ሔራት
አሙኖሞ መስሏት ይህች የኔ እጎት

ስልኩ ጭርር ብሎ ሲደውል ቆየና
እቴ ስታነሳው ዝም አለ አንዳንና

ከዚያ እቴ አለቸ ማንን ፈላጊ ነው
ፍቅረኛ ዬ ይሆን አሁን የደወለው?

ብላ ብትጠይቅ ወንድሜ አንዲህ አለ
የለም የኔ ፍቅር ነቸ የኔሞ አምሳለ!

አማማም በተራ እነሱ አይዳሉም
አለቸ ማኅበርተኖ ቼ ሳይሆ ኑ አይቀሩም

አባቴም በራናው የኔ ጌዳኖ ቸ
ናቸው የደወሉት ምነ ሆነሻል አንቸ?

ብለው በጭቅጭቅ አፍ ላፍ ሲካረቱ
ለኔ ነው ለኔ ነው ብለው ሲጋገቱ

ያ! ያቃጨለው ስልክ መልሶ ጭጭ አስኪል
ከጉረቤት ሔጄ የነበርኩ ስደውል

በጠቡ መሔል በጣልቃ ገብቼ
እኔ ነኝ የደወልኩ አልኩኝ ዘመዴቼ

ጥር 1986 ዓ.ም.

ሐዘኔ ከበደ

አፈር ፈጭተን ስናድግ እዚያ እኖ መንደር
ገደብ ባልነበረው ተሳስረን በፍቅር
እጅ ለጅ ተያይዘን ስንሸረሸር
ምን ብለሽኝ ነበር? ምን ብዮሽ ነበር?

በዛፎች ከለላ አዝማመን ስንሔድ
የአበቦች ሽታ መዓዛው ሲያውድ
እንኳን ጠላትና ሲቀና ዘመድ
ተጋብተን ለመኖር ወልዶን ለመክበድ

ምኖት ሕልማችንን ያኔ ያቀድነውን
ልንፈጽም ካልቻልን ቃል የገባነውን
ዛሬ ቀዝቀዝ ካለ ያ ሁሉ ፍቅራችን
በጣም ያሳዝናል ሰዎች መሆናችን

በወፎች ጫጫታ ልቤ ተመስጦ
ያንቺም ልብ እንዴ ኤው በሃሳብ ተውጦ
በፍቅር ትኩሳት አካላችን ቀልጦ
ጉድ እንዳልተባለ ሚሥጢሬ ተገልጦ

የጋለው ፍቅራችን ዛሬ ከበረዶ
ዳንዴናው ልባችን ለመኖድ ከራዶ
ፍቅርን ያመነ ሰው መሆኑን ያበዶ
በእውን ተረዳሁት ሐዘኔ ከበዶ

1980 ዓ.ም.

አልቻልኩም

(አብሮ መሰዳድ)

የልቤ ሰመመን የፍቅሬ ትዝታ
የዓይኖቼ ብሌን የሕይወቴ አለኝታ

እኔን ከጠላሽኝ ከናቅሽ ፍቅሬን
ከመሔዴ በፊት ስሚማ አሮጮን

ልዝብ አንደበትሽ ታጋሽ ተፈጥሮሽ
አስተዋይ አእምሮሽ ንጹሕ ልቦናሽ

ተባብሮ ከዓይኖችሽ ከውበትሽ ጋር
ልቤን ማርኮ ወስዶ አሰረው በፍቅር

ኮክብ ዓይኖችሽን ጉብል ጉንጮችሽን
የቀጭኔ ጭራ መሳይ ጸጉሮችሽን

ሊጋ ከንፈርሽን ወለላ አንዴግር
ንብረቴ ለማድረግ ምኖቴ ነበር

አይቻልም ካልሽኝ ማቀፍ ሽንጥሽን
እኔ አልፈቅድም ካልሽኝ መሳም ከንፈርሽን

ፍቅሬን መግለጥ ካልቻልኩ የልቤን መንገር
በሰላም አናብታው መጣላት ይቅር

እንሰነባበት ነውና መጊዜ
ጸፈልኝ ቢቻልሽ ትዝ ባልኩሽ ጊዜ

ስለተለበለብኩ በፍቅርሽ ንዴድ
አልቻልኩም ለመኖር አብሮ መሰዳድ

ሐምሌ 1954 ዓ.ም.

ታማሁኝ በፍቅር

የዘንድሮማ ሰው ማውራት ያውቅበታል
ልቡን ወስዴዋለች ብሎ ያዋሽካል

ሔሜተኖቹ እመኝ ደካማ ነው ብለው
መልካም ልጅ ባፈቅር ድካሜ እምን ላይ ነው

ጋጢስት አይደለም ወይ ወንጀል ማፍቀር
አሰቲ ተውኝ ሰዎች በሰላም ልኑር

ለኑሮ መዋተት መውጣትና መውረድ
መቼ አነሰኝና በፍቅር ልዋረድ

ይሽ ሀሜታቸው እንደይሆን እውነት
ተይ አታንገላቺኝ በፍቅር ሽ አልመት

ጥር 1985 ዓ.ም

የቆሰለው ልቤ

የቆሰለው ልቤ እያለኝ አልችል
ዓይኖቼ እንባ ሲያዝሉ አኔ ስታገል

በፍጹም ጭካኔ ፍቅረን ስለጣል ሽ
ተመቸ ሽ ወይ አሁን ዴስ አለ ሽ ደላ ሽ

በረደ እንኳን ሳይጥል ውርጩ ሳይወረዛ
ቁረ ሳይጠ ነክር ምድር ሳይሞላው ጤዛ

ስምሽን ስሰማ ሳስብ ፍቅርሽን
እንዘረዘፋለሁ በብርድ በሔዘን

ሃሳብ ተለዋውጠን ምስጢር ተወያይተን
በክፉ በደግ ቀን እንዴዚያ ተስማምተን

አሁን ብንለያይ እንባ ብንራጭ
ማነው ዴስ የሚለው፣ ማነው የሚቆጭ?

1954 ዓ/ም

በል ክብርዋን መልስ

"ጌታ እንዴምን ዋሉ እንዴት አረፈዱ
ብቻዎን ነሥት ወይ እሜቴስ የት ጌዱ?"

አያሉ ጠይቀው መልሱን አንዳገኙ
ግግለድ ጀመሪ አሽ በጄ ሊያሰኙ

"እዩት ይሽ ወጣት በመልክ ዘለላው
በትምህርት በዓመሉ ዴግሞም በሥራው

በጣሙን ከፍ ያለ ምስጉን ስለሆነ
ባለፈው ወር እንኳን የክፍሉ ሹም ሆነ

ሲጋራ አማያጨስ፣ መጠጥ የማይጠጣ
ጀምበር ከጠለቀች፣ ከቤት የማይወጣ

ቤተክሲያን ሳሚ ነው፣ ፍፁም ጸሎተኛ
ሲጣሉ አስታራቂ፣ ጉብኝ በሽተኛ

ልጅዎን ፀደለን፣ ሞያ አመሏን አውቆ
የርስዎን ዝምድና፣ ስላሻ አጥብቆ

ጋብቻ ሲጠይቅ፣ አድርጌ አግላጅ
ተማምኖ ነው በኔ፣ በርስዎ ወዴጅ

ልክ እንደልጄ ነው፣ ሳምነው ስወደው
የሰጋ ዝምድና፣ እናጣም እንዲያው

ስለዚህ በሞቴ፣ በፍቅራችን አምላክ
ይዳራለት ለሱ፣ ዘርም ይባረክ!

ፀደለን ለማግባት፣ ከጠየቁት ሁሉ
አቻ ይመስል ነበር፣ በግብረ ባመሉ

እንዲሁም ከመጡት፣ ብዙ አማላጆች
ከእኔህ ጋር ነበሩ፣ በጣም ወዳጆች

የከፍሉ ሹም ሆኖ፣ ከታጨማ በአንዴ
ይረዳኛል ብለው፣ ይጠቅማል ለንግዴ"

"እሽ! ምን ከፍቶኝ" አሉ፣ "ቀኑ ይወሰን
ፈቅጄለሁ እኔ፣ ያግባት ፀደለን"

በተወሰነው ቀን፣ አጥር ግቢው ደምቆ
ድንኳኑ በመብራት፣ በአበባ አሸብርቆ

ድም ድልቅ አታሞው፣ ሲነዛ ክብሯን
በአጀብ በአልልታ፣ ዳሯት ፀደለን

ፀደለና ጉበኛው፣ ባልና ሚስቱ ቹ
ለመልስ የመጡለት፣ ከነሚዜም ቹ

የፀደለ አባት፣ አቶ ይትባረክ
ጉበኛውን ጠሩና፣ ጀመሩ መስበክ

"ስማኝማ ልጄ፣ ላዋይህ ምስጢር
አኔ እንደምታውቀው፣ አለኝ ብዙ ብር

ግና ሠራተኖቼ፣ ባዕዶች ስለሆኑ
ሊያከሳስሩኝ ነው፣ እያበካከኑ

ከዛሬ ጀምሮ፣ እንግዲህ ዕውቀው
ንግዱም ሆነ ሀብቴ፣ እንዳንብረትህ ነው

ስለዚህ ከሥራህ፣ ለቀህ ተሰናብተህ
መጥተህ አዘገጃጀት፣ በንብረቴ ገብተህ"

ጉበኛውም ብልህ ሰው፣ ብርቱ ነበርና
ሰመረለት ንግዱ፣ ሔዳለት በጅህና

ሸቀጣ ሸቀጡን፣ ከውጭ ከማምጣት
ፋብሪካ አቋቁሞ፣ ጀመረ መሥራት

ከዕለታት አንድ ቀን፣ አንድ ግብዣ ቦታ
ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ደምቆ ሳቅ ጨዋታ

ትንሽ ሞቅ ያለው ሰው ከመሃላቸው
"ሰማህ ወይ ይትባረክ! አማችህ ይህ ነው?

ዶኃ ወገነ ቢስ፣ ዘረ ያልታወቀ
ወጥ ቀታይነቱ፣ ሽታው ያስታወቀ

ትድራት ወይ ለዚህ! ለአሳላፊ አለቃ!
የአንድ ወር ደሞዙ፣ ለውስኪ አማይበቃ!"

የፀደለ አባትም፣ ነገሩን ሰምተው
በጉብኝው ዘር፣ ማንዘር፣ አፍረው በጌሣው

"አታሎኝ፣ ደልሎኝ፣ ጋብቻ ሲጠይቅ!
በጣም ያሳዝናል፣ የኔ አለማወቅ!"

የባል፣ የሚስት ልብ፣ በፍቅር ሲነድ
"ሰምቼ አላውቅም አንዲህ ያለ ጉድ"

አያሉ "አሚቆጪኝ፣ ክብርዋን መውሰዱ ነው"
ብለው አፋቱዋቸው፣ በዚሁ ተናደው

"አንተ አጭበርባሪ፣ አንተ ግብስብስ!"
አሉት፣ "ቀስ ብለህ ሕጋንም መልስ!"

1940 ዓ/ም

ምዕራፍ ፫

ግብረ-ገብነት

አንቃወማቸን፡



ገበሬ ነበር የተማረከው
አሁን ይተምናል ሰውንድ ምሳሌ
ይተንና ሰሐራ ሸፈነ ሕዝብ
ቀይ ፡ ቀይ ፡ ቀይ አያሉ አንሰማቸውም

ምዕራፍ ፫

ግብረ-ገብነት

ጣቶ ቸህን ዘርጋ	83
ሰብቀኛ	84
ማን ውሀ ይስጣ ቸሁ	87
ትልቅ ቅርስ	89
ራቢንድራናት ታጐሬ	90
ችግር	91
ለሁለት ሁናቴ	92
ምረት	92
አጋጣሚ	93
ምሥጢር	95
ከአዳም ያልመጣ	95
ምነው እኛ ብቻ	96
ለሰውነቱ ክብር	97
ብቸኛ ሻማ	98
ገንዘብ	100
የማን ጀከስ ጣጣ	101
ዲሞስቴ ኔስ	104
ፈፈቴ	106
ማሞ ከየት መጣህ	107
ማሚት ከየት መጣሽ	109
ኑዛዜ	111
አቂም	112

ጣቶ ቸህን ዘርጋ

ጣቶ ቸህን ዘርጋ ይበላለጣሉ
አጭርና ረጅም ሁነው ይታያሉ
ከቀጭኖ ቹ ጎን ወፍራሞ ችም አሉ
ጨብጣ ቸውና አኩል ይሆናሉ

በሕይወት ዓለም ውስጥ አኖም ስንኖር
አብዛኛው ሲቸገር ጥቂቱ ሲከብር
ገሸ ቁጭ ብሎ አራሽ ቢያስገብር
የሰው መብት ገፍፎ ቢመዘባበር

ቢዘነጋው እንኳን ለጨቋኝ ወገን
ወጣትና አዛውንት ወፍራም ወይ ቀጭን
የተወለድንና የምንሞት ቀን
የማንበላለጥ አቻ እንደሆንን

ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ የሰው ልጅ ፍጡር
ከእንዲህ ወዲያ በኢትዮጵያ ምድር
ሊኖር እንዳማይችል በመንቀባረር
እናስተምራቸው በመተባበር

ጥር 1985 ዓ.ም

ሰብቀ ኛ

ስሙን የማልጠቅሰው አገሌ የሚሉት
ሰውን ያሰለቸ የወረ ባላባት
አንድ ሰው ነበረ የሆነኝ ጎረቤት

አሉባልታን መንዛት ቆጥሮ አንደ ሥራ
የጣሙን የቆጡን ሐሰት እያወራ
አንዱን ካንዱ አጣልቶ በመፈፀም ሴራ

ሲያምታታ ሲደልት ሞቶ በድንገት
በታረዛ ታዝሎ ሲደርስ ሐኪም ቤት
በሰው ሠራሽ ትንፋሽ ነፍስ ዘረለት

ዓይኖቹ ተገልጠው ሲሉ ክብልልል
የተዘጋ ላንቃው ከፈትፈት ሲል
አተጋደመበት ከራስጌው በኩል

ያለምንም ጥፋት ወንጅሎ በሐሰት
ያሣሠረው ሐኪም የዛሬ አሥር ዓመት
ነበርና ለካ ነፍሱን ያዳነለት

መረቱ ቁና ሆነች በጣም ደነገጠ
በሐፍረት በስጋት ጨርሶ ተዋጠ
ላብ ስምጥ አረገው ዓይኑን አጎረጠ

ወንጅ ዮቃታለሁ እርስም ባልሠራት
በጣሙን ስላፈር ኩ ስላዘንኩ በዕውነት
አሁን ምን ባደርግ አገኛለሁ ምሕረት?

ብሎ ቢጠይቀው ያዳነውን ሐኪም
ሐኪሙም መለሰ ስማኝ የኔ ወንድም
አንድ የላባ ትራስ አምጣና ከየትም

ምረሀት ታገኛለህ ታርፋለህ ከጣጣ
ብሎ እንደመከረው ከዘመዱቹ ዘንድ ትራሱን አስመጣ
ቀጥሎም ጠየቀ ሌላስ ምን ምን ላምጣ?

ሐኪሙ መለሰ ሰንጢ ቢጤ ካለ
ትራሱን ሸርጠተህ እንዲሁ እንዳለ
በትነህ ጨርሰው ላባ እወስጡ አስካለ

ልክ እንዳታዘዘው ላባውን በተነው
ላባውም ተነነ ከተማውን ሞላው
መልሶም ይኸኑ ለሐኪሙ ነገረው

በጣም ጥሩ አርገሃል ትዕዛዜን ማክበርህ
በል አሁን ዳግሞ ሌላ ትዕዛዝ ልስጥህ
የተበተነውን ላባ ሁሉ አምጥተህ

ትራስ ሰፋውና ውጤቱን ስጠኝ
በሐሰት ውንጀላ ስለአሣሠርከኝ
ይህ ካሣ ዮ ይሁን ቅሬታ አይኑረኝ

ብሎ ቢናገረው ሐኪሙ ይህን ቃል
ላባ ለመሰብሰብ አላይ እታች ሲል
ውሎ አመሸና ጀምበር ጥልቅ አስኪል

አፍኝ የማይሞላ ላባዎች ሰብሰባ
የድካሙ ዋጋ ሆኖበት ትርፍ አልባ
ተስፋ ቆረጠና ሐኪሙ ዘንድ ገባ

ሊገልጥ ለሐኪሙ ሲጀምር ትረካ
ሐኪሙ ተዝናንቶ ፊቱን አር ጉ ፈካ
አየው እንደ ዚህ ነው የሔሰት ውሸ ካ

ክብርና ዝና ዮን በመግፈፍ መብቴን
በሔሰት በውሸ ት አጥፍተሽው ሰሜን
ባልፈጸም ኩት ድርጊት ወንጀለሽ ኝ አ ኔን

የአንተ ውንጀላና ያንተ ሚራ ጠንቅ
ልክ እንደላባው ነው ተለቅሞ አማያልቅ
ዳግመ ኛ እንዳይለምድህ ተእንግዲህ ዕወቅ

ብሎ መከረና ያንን ሰባቂ ሰው
ሊቀየም ሊያኮርፈው ሃሳብ እንዳ ሌለው
ገለጠለትና ይቅር ለእግዜር አለው

ግንቦት 1984 ዓ.ም.

ማን ውኃ ይስጣ ችሁ

ባቡርና አውቶቡስ ቢሰክሌት መኪና
ሠራተ ኛን ሁሉ አዝለው ይመጡና

ኒውዮርክና ለንደን፣ ቶኪዮ ፓሪስ
ጥለው ይሄዱ ጊዜው አስቲደርስ

ስፍራ ለማባታት ለብዙ ሚሊዮን
ከተማው ሲቀየስ ትልሙ ሲወሰን

ደርቡ በደርቡ ላይ የባቢሎን ግንብ
ይካባል መኖርያ ይሠራል ለሕዝብ

አጥር ግቢ ቤሱ ሰማይ ጠቀስ ቤት
ዙሪያው መንገድ ብቻ የሌለው አትክልት

በመሆ ኑ አሰል ቺ ከልማት የራቀ
ሰው ዘዴ አገ ኘ በጣም የረቀቀ

በግሰሮ በአፍላል ወይም በወጭት
ቆርቆሮ ለብሙ ሳጥ ኑን ከአንጨት

ከሞላ በኋላ ለም አፈር ፈል ጉ
ያ ሻውን አበባ ይተክላል አች ጉ

ጧት አሥራው ሲሄድ ማታ ቤት ሲመጣ
በቀን ሁለት ጊዜ ውኃ አያጠጣ

በእንዲህ መንከባከብ ያደገው አበባ
እፀብ ነው ውበቱ አንጀት የሚገባ

ግን መድረሱ እማይቀር መጥቶ ቁርጡ ቀን
ሲወስድ ባለቤቱን ሊፈጽም ቃሉን

የአፍላል የማሰር ደግሞም የወጭት
ማን ውኃ ይስጣቸው ለነዚያ አትክልት

ጥር 1964 ዓ/ም

****

የሰው ልጅ በለቅሶ መወለዱን ሲያበስር
እያደገ ሲሔድ በቋንቋ ሲናገር

ከዚያም በዕድሜው ጉዞ ሲወጣ ሲወርድ
ሲመላለስበት ወልደ ሲዋለድ

ከኖረ በኋላ ለውስን ዘመናት
ሙቶ የተኛለት በለቅሶ መሸኘት

ከአዳም ከሔዋን ለወረሰነው ፍዳ
መክፈሉ ይሆን ወይ የድርሻውን ዕዳ!

የካቲት 1985 ዓ/ም

ትልቅ ቅርስ

ሕመሜ ጠንካራ ቲቢ የሚባል
ነበርና ክፉ በጣም የሚያስል
ያለ አንድ አሜዋች ወይንም ደባል
ተሰጠኝ አንድ አልጋ ለብቻ ክፍል

አዚያ ባደ ክፍል ተጋድሜ ሳለ
ሞው አለ ሃሳቤ ሄዶ ኮበለለ
ቅርሴን ለሰው ነዛው አያዳላደለ
ይህ ላንተ፣ ይህ ላንቱ፣ ይህ ላንቺ እያለ

ከብዙ ጥቂቱን አስቲማ ስሙት
ዓይኑ ለታወረ የሙዚቃን ስልት
ጀሮው ለማይሰማ የምድርን ውበት
ሁለቱንም ላጣ የፀሐይ ሙቀት

ሽባና አንካሳው የሌለው አግር
ይውሰድ በቅሎ ፈረስ በደንብ የሚሰግር
እጁ ዱሽ የሆነ ቆማጣ ኩምትር
ይሂድበት በአግሬ ዓለምን ይዙር

በብርድ በሽታ ሳምባው የተነካ
ነፋስ ሲያስጉነብስ ሾላ ወይም ዋርካ
አይቶ ዳስ ይበለው ሰውነቱ ይርካ

ሆዱን ኩላሊቱን ለጉረባበጠው
ጠበልን ይጠጣ መድሔኒቱ ያ ነው
ዳዊው ያልታወቀ ናላውን ያዞረው
ፈዋሹ ፈጣሪ እሱ ይታደገው

ከእነዚህ አንዱ እንኳን ያል ጉዳለው ጀግና
ሸረ ለምን ይዘን ምን ጠነቀውና
ሕይወት ምኞት ያለው ሰላምና ጤና
ይሥራ ለወገኑ ቆርጦ ይነሳና

ጳጉሜ 1944 ዓ/ም

ራቢንድራናት ታጎሬ

የታጎሬ አሽከሪ ቁርስ የሚያሰናዳ
ልብስ የሚጠርግለት ቤቱን የሚያፀዳ
ያለወትሮው ቆየ ሳይመጣ ማለዳ

እንዲህ መዘግየቱ ስላናደደው
በየሰኮንድና በየደቂቃው
አበራ ላይ ሁኖ ቆሞ ጠበቀው

ሲያወጣና ሲያወርድ የቅጣቱን ዓይነት
ሁለት ሰዓት ያህል ስለዘገየበት
አሰበ አሽከሩን ከሥራ ማስወጣት

ይህንን ወስኖ ሲጀምር ሊወጣ
አሽከሩ ወዲያው ኑ አቤት እንደመጣ
ጀመረ ሊያዘጋጅ ዕቃ ሊያወጣጣ

ታጎሬም ተናደ ግሎ ስለነበር
በል ቀስ ብለህ ውጣ በመጣህበት በር
ብሎ አሰናበተው ያንን ምስኪን አሽከር

አሽከር ግን ለጊዜው ያልሰማ ሰው መስሎ
ሲጨርስ አጽድቶ ሁሉን አስተካክሎ
ጀመረ ሊያሰረዳ ጌቶች ስመኝ ብሎ

ትናንትና ሌሊት ድንገት በውድቅት
ትንሿ ሕፃኔ ታማ ብትሞት
ለቀብር ሄጄ ነው ያለፈው ሰዓት

ብሎ ወዲያው ኑ ቢወድቅ አግሬ ስር
ሊለምነው መስሎት ይቅርታ ወይ ብር
አቃተው ለማንሳት ቢጥር ቢሞክር

እንዲህ በድንገት ስለሞተ አሽከሩ
ታጎሬ ተነክቶ ሲያዝን በነገሩ
ይሸዋ ታሪኩ ተጸፈ ባጭሩ

1952 ዓ/ም

****

በሰው ላይ ለመፍረድ እንዳንቻ ኩል
ጉዳዮን ማጣራት ሂሳብ መቀበል
ተገቢ ነውና በተግባር ማዋል
ይሸንን ትረካ እናጢን በውል

1952 ዓ/ም

ችግር

ችግርና አዳጋ ይደርሳል በቅጽበት
ችግርን ለመቅረፍ ያለፋል ዘመናት

ይህን ለመሰለ አክል ላጋጠመው
ፈጥኖ የደረሰ አለሁልህ ያለው

የሰማይ ቤቱን ጽድቅ የምድሩን ክብር
ይጎናጸፈዋል ከራስ አስከ እግር

ጥር 1985 ዓ.ም.

ሁለት ሁናቴ

የሰው ልጅ በሕይወት ጉዞ
ላይና ታች ሲከርም ናውዛ

ሲሆን በፍቅር አለያም በጠብ
በመጪ ነቅ በመጠበብ

አንዱን ሲወድ ሌላውን ጠልቶ
ከዚያ ሲሄዝት ከዚህ ተስማምቶ

ይከርምና አርጀት ሲል
ይጀምራል ማሰላሰል

ይሽ ሁሉ ውጣ ውረድ
መከበረ ወይ መዋረድ

ሁለት ሀናቴ ሁለት ሐቅ
ለምን ይሆን ብሎ ቢጠይቅ

ለሚያልፍ ጊዜ ለሚያልፍ ዓለም
መልሱ ይሁን ከንቱ አይድከም

1959 ዓ/ም

ምሬት

መጫምያ አጣሁ ብዬ እኔ ስማረር
እግር የሌለው አየሁ ወይ የዓለም ነገር

ጎደር 1969 ዓ.ም.

አጋጣሚ

ወዳጅ ሲበታተን ጠላት ሲከማች
ከፋ ሰው ሲወደድ ዳግ ሰው ሲተች

የሚጠሉት መጥቶ የሚወዱት ሲቀር
አጋጥሞዋች ሁ ይሆን አንዲህ ያለ ነገር

በዕድል በአጋጣሚ በሚሆነው ሁሉ
ከገቡበት ሳንካ መውጣት የማይችሉ

ካለፈው ስሕተቱ የማይማር ሰው
አጋጥሟች ሁ ይሆን አንዲ ዚህ ያለው

በዕድል ባጋጣሚ ችግር ውስጥ ቢገባ
ለማላቀቅ ሲሆን ግራ የሚያጋባ

የተወሳሰቡ የኑሮ አባዜ
አጋጥሟች ሁ ይሆን ባለንበት ጊዜ

ይህንና ይህን ይህን የመሰለ
በ ኑሮ ኂዳት ውስጥ ብዙ ሳንካ አለ

አለፍ አለፍ ብሎ ግን በአጋጣሚ
ጥቅም ሰጪ የሆነ ለሰው ልጅ ተስማሚ

ትካዜን በደስታ ለውጦ አሚሰጥ
ማጋጠሙ አይቀርም በዓለም ጉዞ ውስጥ

ይህን የመሰለ ብዙ አጋጣሚ
እኔም ደርሶብኛል በተደጋጋሚ

የአራት ዓመት ወጣት የመለሰው መልስ
በጣም ይገርመኛል እስካሁን ድረስ

ማሙዬ ስታድግ ምን ትሆናለህ
ብዬ ብጠይቀው አለኝ አንዴ ዚህ

"አባባ ሲያስቡት ምን ልሆን ልመኝ"
"ያው እንዳሌላው ሰው ትልቅ ነዋ!" አለኝ

መጋቢት 1976 ዓ.ም.

ምሥጢር

ምሥጢር ነው ያልከውን ለሌላ ሰው መንገር
መሆኑን ተረዳ በገዛጅ መታሠር

ግን ምሥጢር ለባዕድ አስካልተነገረ
ምሥጢርህ ምሥጢር ነው ባንተው ከታሠረ

ምሥጢርህን ሌላ ሰው ካየና ከሰማው
ያባከንከው ምሥጢር ላንተ ዘብጥያህ ነው

ሕዳር 1985 ዓ.ም.

ከአደም ያልመጣ

ለወንድና ለሴት ለአዳም ልጆች
ሔዋን በበኩሏ እናታቸው ነች

ብለን ብንገምት ብንገመግም
አዳምና ሔዋን በአገኙት መርገም

አዳም አርሻውን ሲያርስ ሔዋን ስትፈትል
ግን ነበረች ልዕልት ግን ነበረ ልዑል

መኳንንት መሳፍንት ከየት ተፈጠረ
ከአዳም ያልመጣ ግንዱስ የትነው ዘረ

ኅዳር 1953 ዓ.ም.

****

እግዚር ሞትን ሲልክ ወዳ ሰዎች ቤት
ወራሾች ተንጋግተው በአጀብ ሸኙት

ምነው እኛ ብቻ

እንጨትን በእንጨት ቢቦረቡሩት
ይጨሳል ይነዳል ይሆናል እሳት

እሳት ተፋፍሞ ቢያቃጥል ቤት ዶንን
መድኃኒት ውሀ አለ ቃጠሎ አሚያዳፍን

በአፍላል ተጥዶ ውሀ ቢፍለቀለቅ
እንፋሎት ይሆናል ከአየር ሊዳባለቅ

በእሳት ቢለበለብ ድንጋይና አፈር
ይሆናል ስሚንቶ ብረትና ብር

ምሳር ከተሠራ ተቀጥቅሞ ብረት
መልሶ ይቆርጣል ብረትና እንጨት

ቅር ጹን አስተካክለው የእንጨት የብረት
ባቡር አይሮፕላን መርከብ ቢሠሩት

እንፋሎት በብልሃት ከተጠራቀመ
ሁሉም በየዘዴው ከተገጣጠመ

ይሽከረከራሉ ሕዝብ ለማጓዝ
እሳት ብረት ውሀ በመተጋገዝ

እሳት ብረት አቅላጭ እንዲሁም ውሀ አፍይ
ውሀም የእሳት ጠላይ ብረት እንጨት ጣይ

ሶስቱ ባላንጣዎች እሳት ውሀ ብረት
መታ ላይ ከዋሉ ተስማምተው በጎብረት

የጋንዲና ሱዳን ሱማሌ ኢትዮጵያ
ግላዊና ዛኢር ጋናና ናይጄርያ

ምንው እኛ ብቻ ያለነው አፍሪካ
ከተማ ባላገር የምንኖር በጫካ

ሰበብ እያረግን በቋንቋ በጎሳ
ሕዝባችንን በጎ ሰላም የምንነሳ!

